ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ ሰብ ኮሌጅ

የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

# “ቴሎስ ረጅም ልብ ወለድ ከልብ ወለድ አላባዊያን አንጻር”

በ

አበባው አበበ

ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ 2014 ዓ.ም

# “ቴሎስ ረጅም ልብ ወለድ ከልብ ወለድ አላባዊያን አንጻር”

በ

አበባው አበበ

የጥናቱ አማካሪ

መምህር ሽኩር ናስር

ለትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለባችለር ኦፍ አርትስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ

ጥናታዊ ጽሁፍ

ሰኔ 2014 ዓ.ም

# የአማካሪዉ ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፁሁፍ በወልቂጤ ዩነቨርስቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመርያ ድግሪ ማሟያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆነን አረጋግጣለሁ።

የአማካሪዉ ስም___________________________________

ፊርማ_________________________________________

ይህ ጥናት በተማሪ አበባው አበበ "ቴሎስ ረጅም ልብ ወለድ ከልብ ወለድ አላባዊያን አንጻር" የመጀመርያ ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፁሁፍ ሲሆን የዩንቨርስቲዉን ጥራት ደረጃ የሟላና በቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆነን ማረጋገጫ ነዉ።

ፈታኝ አንድ____________________________________ፊርማ

ፈታኝ ሁለት____________________________________ፊርማ

ቀን________________________

## ሙዳየ-ቃላት

- ቴሎስ፡- አንድ ነገር የተፈጠረበት አላማ
- ሚሎሪና፡- ሚስጥራዊ ክታብ

# ምስጋና

ከሁሉም በላይ ሁሉንም ለሚያሳልፈው ለቅድስት ድንግል ማሪያም ልጅ ከናቱ ጋር ይክበርልኝ። በመቀጠልም ክፍተቴን ለሚሰፉልኝ እንዲሁም ከፍታን ለሚመኙልኝ ቤተሰቦቼ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው። በመጨረሻም ይህን ጥናት የተሻለ እንዲሆን ከጎኔ አብሮኝ ማስተካከያ እየሰጠ ላበረታኝ መምህሬ ፤ ለመምህር ሽኩር ናስር ምስጋናዬ ይድረስ።

# አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ "ቴሎስ" ረጅም ልቦለድን ከልቦለድ አላባዊን አንፃር ተንትኖ የሚያቀርብ ነው። ስለሆነም አጥኝው "ቴሎስ" ረጅም ልቦለድን ከልቦለድ አላባዊያን አንፃር ተንትኖ አቅርቧል። አጥኝው ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስ ለጥናቱ መነሻ የሆነውን ልቦለድ ደጋግሞ በማንበብና ሌሎችም ሃሳባቸው በልቦለድና በምርምር ዙሪያ የተፃፉ መፅሃፍትን በመቃኘት ነው። በነዚህም መፅሃፍት ተመርኩዞ "ቴሎስ" ረጅም ልቦለድን ከአላባዊን አንፃር ተንትኖ በጥናቱ ውስጥ አስፍሯል።

# ማውጫ

ርዕስ

ገጽ

ሙዳየ-ቃላት ........ I
ምስጋና ........ II
አጠቃሎ ........ III
ምዕራፍ አንድ ........ 1
1.መግቢያ ........ 1
1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 1
1.2. የጥናቱ አላማ ........ 1
1.2.1. የጥናቱ ዋና አላማ ........ 1
1.2.2. የጥናቱ ንዑስ አላማ ........ 2
1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 2
1.4. ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ........ 2
1.5. የጥናቱ ወሰን ........ 2
1.7. የጥናቱ አወቃቀር ........ 3
1.8. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው ........ 3
ምዕራፍ ሁለት........ 5
2.1. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ........ 3
2.2. ረጅም ልቦለድ ........ 4
2.2.1. ገፀባሕርያት ........ 4
2.2.2. የገፀባህርያት አይነቶች ........ 5
2.2.3. መቼት ........ 8
2.2.4. ጭብጥ ........ 8
2.2.5. ታሪክ ........ 9
2.2.6 ትልም ........ 9
2.2.6. አንፃር ........ 9
2.3. የተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፍ ቅኝት ........ 11

ምዕራፍ
ሶስት…………………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………… ….15

3. የመረጃ ትንተና ..........................................................................................................13
3.1. የቴሎስ ረጅም ልቦለድ ጭምቅ ታሪክ ......................................................................13
3.2. ቴሎስ ረጅም ልቦለድ ከትልም አንፃር ......................................................................14
3.3. ገፀ-ባህርያት በቴሎስ ረጅም ልቦለድ .........................................................................15
3.3.1. የያሬድ የገፀ-ባህሪ አሳሳል በቴሎስ ረጅም ልቦለድ.......................................................15
3.3.2. የወርቄ የገፀ - ባህሪ አሳሳል በቴሎስ ረጅም ልቦለድ...................................................15
3.3.3. የመስፍን የገፀ - ባህሪ አሳሳል በቴሎስ ረጅም ልቦለድ .................................................16
3.3.4. የአባ ላዕከ ማርያም የገፀ-ባህሪ አሳሳል በቴሎስ ረጅም ልቦለድ......................................16
3.3.5. የአሊሰን የገፀ-ባህሪ አሳሳል በቴሎስ ረጅም ልቦለድ.....................................................16
3.3.6. የሊንዳ የገፀ ባህሪ አሳሳል በቴሎስ ረጅም ልቦለድ .......................................................17
3.3.7. የታቤል የገፀ-ባህሪ አሳሳል በቴሎስ ረጅም ልቦለድ.......................................................17
3.4. ቴሎስ ረጅም ልቦለድ ከግጭት አንፃር.......................................................................17
3.5. ቴሎስ ረጅም ልቦለድ ከጭብጥ አንፃር .......................................................................18
3.6. ቴሎስ ረጅም ልቦለድ ከመቼት አንፃር.......................................................................19
3.8. የቴሎስ ረጅም ልቦለድ ጠንካራ ጎን ...........................................................................21
3.9. የቴሎስ ረጅም ልቦለድ ደካማ ጎኖች.........................................................................21
ምዕራፍ
አራት………………………………………………………………………………………………
……………………………………………………………………… 26

4.ማጠቃለያ ..................................................................................................................23
4.1.የመፍትሄ ሀሳቦች .......................................................................................................24
ዋቢ-መፅሃፍት .................................................................................................................

# ምዕራፍ አንድ

# 1.መግቢያ

ልቦለድ በእንግሊዘኛ ቋንቋ "NOVEL" የሚለውን የስነ-ፅሁፍ ዘርፍ እንዲወክል የተመረጠ ስነ-ፅሁፋዊ ስያሜ ነው። ልቦለድ ምንድን ነው? ለሚለው የመነሻ ጥያቄ አንድ ቁርጥ ያለ ሁል አቀፍ ብያኔ መስጠት አዳጋች ይሆናል። ይህ የስነ-ፅሁፍ ዘር ከታየበት ከ18ኛው ክፍለዘመን ወዲህ የተነሱ አያሌ የስነ-ፅሁፍ ሃያሲያንና ደራሲያን ከሚያደርጉት የስነፅሁፍ ትንታኔና አላማ፣ምክንያት ፣ባህሪና አቀጣጫ አንፃር ሃሳባቸውን ሰጥተውበታል ። ዘሪሁን አስፋው የስነፅሁፍ መሰረታዊያን እንዲህ ሲል ገልፆታል። ''ልቦለድ ከደራሲው ምናባዊ ፈጠራ የሚመነጭ፣የሰውን ህይወት ልዩ ልዩ መልኮች በተመሳሰሎ ለመቅረፅ የሚያስችል በቁሙ ግን እውነት ያልሆነ ኪነጥበባዊ ስራ ነው ። ልቦለድ በእውኑ አለም በሰዎች የህይወት ገጠመኝ ከተፈፀመው እና ሊፈፀም ከሚችለው በከያኒው ግንዛቤና አመለካከት ተቀምሮ የሚቀርብ የማህበረሰቡ ቁሳዊ እና ህሊናዊ ገፅታ የሚታይበት ኪነታዊ ስራ ነው።'' (2005፤152)

ልቦለድ አጭርና እረጅም ተብሎ በሁለት ይከፈላል። አጭር ልቦለድ ሰብሰብ ያለ ወይም የታመቀ ጠባቃ ትስስር ያለው ፈጣንነት ጎልቶ የሚታይበትና የሁሉም ነገር መቋጫ የሆነ ትኩረት ያለው ነጥብን የሚያጠነጥን የልቦለድ አይነት ነው። ዘሪሁን አስፋው የስነፅሁፍ መሰረታዊያን (2005፣229)

ሌላኛው የልቦለድ አይነት ረጅም ልቦለድ ሲሆን ብርሃኑ ገብረፃዲቅ "አጠቃላይ የአማረኛ ቋንቋ" በተሰኘው መፅሃፌ እንዲህ ሲል አስፍሮታል፣ "ረጅም ልቦለድ ብዙ ገፀ ባህሪያትን የሚያሳትፍ ታሪኩ በተለያዩ ቦታዎችና በተለያዩ ጊዚያት የሚፈፀም፣ሰፊና ውስብስብ ግጭቶችን የሚይዝ፣ብዙ ቅርንጫፍ ጭብጦችን የሚይዝ እና ብዛት ባላቸው ገፆችና ከሰሚኒያሽህ ባላነሱ ቃላት የሚፃፍ የልቦለድ አይነት ነው። (2008፣109) ይህ ጥናታዊ ፅሁፍም "ቴሎስ" ረጅም ልብወለድን ከልቦለድ አላባዊን አንፃር ተንትኗል።

## 1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚው ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ለማጥናት ያነሳሱት ምክንያቶች በልቦለዱ ዙሪያ የተሰሩ ሌሎች ጥናቶች እንዳለመኖራቸው መጠንና ልቦለዱ አዲስ ስራ እንደመሆኑ መጠን የተገነዘበትን መንገድ ከአላባዊን አንፃር መተንተንና መገምገም ስለፈለገ ነው።

## 1.2. የጥናቱ አላማ

### 1.2.1. የጥናቱ ዋና አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ "ቴሎስ" ረጅም ልቦለድን ከረጅም ልቦለድ አላባዊያን አንፃር መተንተን ነዉ ።

## 1.2.2. የጥናቱ ንዑስ አላማ

**የጥናቱ ንዑስ አላማዎች፡-**

- የልቦለዱን አብይ ክፍተቶች እና ጠንካራ ጎኖች ከአላባዊያን አንፃር በማስርጃ መተንተን
- የልቦለዱን ዋና ሃሳብ መግለፅ
- ለልቦዱ ክፍተቶች የመፍትሄ ሃሳብና መላምንት መስጠት ነው ።

## 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ በልቦለድ ዙሪያ ለሚያጠኑ የምርምር አካላትም ሆነ በሌላ ልቦለድ ላይ ጥናት ለሚሰሩ ሰዎች ሁሉ እንደ እንደ መረጃነት ያገለግላል፡፡ በተጨማሪም ለጀማሪ ደራሲያን ስለ ልቦለድ አላባዊን እውቅና እንዲሁም ስለቴሎስ ረጅም ልቦለድ ግንዛቤ ይሆናል ።

## 1.4. ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

- የቴሎስ ረጅም ልቦለድ የልቦለድ አላባዊያንን አዋቅሯል ወይ?
- የልቦለዱ ዋና ሃሳብ ምንድን ነው?
- የልቦለዱ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች ምንድን ናቸው? የሚሉትን ሃሳቦች ያነሳል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በደራሲ ናሁሰናይ ፀዳሉ በ2014 "ቴሎስ" በተሰኘ ርዕስ የቀረበን ረጅም ልቦለድ ከልቦለድ አላባዊያን አንፃር ማለትም፣ከጭብጥ፤ገፀባሕርያት፣ታሪክ፣መቼት፣ግጭት፣ትልምና አንፃርን ተንትኗል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ገላጭ የምርምር አይነትን የተከተለ ነው፡፡ አለም እሸቱ መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ ዘዴ (2001፣148) "ገላጭ ምርምር ገለፃን፣ትንታኔንና አተረጓጎምን መሰረት የሚያደርግ ሲሆን በሁለት ተለዋዋጮች መካከል የሚኖረውን ተዛምዶ እያወዳደረና እያነፃፀረ ይመለከታል፡፡" ያለው እንዳወቅም የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር በተሰኘው መፅሃፉ ገላጭ የምርምር አይነትን እንዲህ ሲል አስፍሯል ፣ "ገላጭ ምርምር ስሙ እንደሚያመለክተው ተመራማሪው አንድ ጉዳይ አንስቶ ችግሩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መሠረት አድርጎ በትረካዊ መንገድ የሚያቀርብበት ነው" (2009፣21) አጥኝው ገላጭ የጥናት አይነትን በመጠቀም "ቴሎስ" ረጅም ልቦለድን ከረጅም ልቦለድ አላባዊያን አንፃር ተንትኗል፡፡

### 1.6.1. የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ማነኛውም ጥናታዊ ፅሁፍ የጥናቱ አይነት እና ጥናቱን ለመስራት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ይኖሩታል። አጥኝው ይህን ጥናት ለመስራት የተጠቀምበት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መዛግብትን ነው።

### 1.6.1.1. **መዛግብት** (Documents)

መዛግብቶች በፅሁፍ ደረጃ ሆነው ለህትመት የበቁም ሆነ ያልበቁ መረጃዎች ናቸው። ያለው እንዳወቀ ሙሉ "የምርምር መሰረታዊ መርሆዎች እና አተገባበር " በሚለው መፅሃፉ ውስጥ፤ "መዛግብት ተመራማሪው ስላለፈም ይሁን ወቅታዊ ጉዳይ መረጃ ለመሰብሰብ ሲነሳ ሊጠቀምባቸው የሚችሉ ጠቃሚ ነገሮች ናቸው። መዛግብት በፅሁፍ መልክ ከየቤተመፅሃፍቱ፣ከየቤተመዛግብቱ ወይም ከሌሎች መሰብሰቢያ ቦታዎችና እንደሁኔታውም ከግለሰቦች ሊገኙ የሚችሉ የመረጃ ምንጮች ናቸው። “(2009፣91) አጥኝው ይህን ጥናት ለመስራት የተለያዩ መዛግብትን ዳሷል። ከነዚህም መካከል እነደ ጥናታዊ ፅሁፎች፣የመማሪያ መፅሃፍት፣ልቦለዶችን፤ቴሎስ ረጅም ልቦለድንና ድህረገፆችን ተጠቅሟል።

## 1.7. **የጥናቱ አወቃቀር**

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በአራት ዋና ዋና ምዕራፎች የተከፈለ ነው። በምዕራፍ አንድ መግቢያ ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አላማ፣የጥናቱ ጠቀሜታ፣የጥናቱ ወሰን ፣ የጥናቱ ዘዴ፣በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሄዎቻቸውን አካቷል። በምዕራፍ ሁለት ንድፈሀሳባዊ ቅኝት እና የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝትን ይዟል። በምዕራፍ ሶስትም የመረጃ ትንተና ማለትም "ቴሎስ" ረጅም ልቦለድን ከእያንዳንዱ አላባዊያን አንፃር ማብራሪያ ሰጥቶ ክፍተቶችን ጭምር ያትታል። በምዕራፍ አራት ደግሞ የማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳቦች እንዲሁም ዋቢ መፅሃፍትን አጠቃኋል።

## 1.8. **በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው**

አጥኝው ጥናቱን በሚያጠናበት ወቅት ስለ ልቦለድ የሚያብራሩ መፅሃፍትን በፈለገው መጠን ማግኘት አልቻለም ነበር። ይህንን የመፅሃፍት ችግር ከግቢው መፅሃፍት ቤት ውጭ በሆኑ ልዩ ልዩ የመረጃ ቦታዎች በማፈላለግ ተጠቅሟል።

# **ምዕራፍ ሁለት**

## 2.1. **ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት**

ጥናቱ ከረጅም ልቦለድ ባህርያት አንፃር ስለሆነ በተመሳሳይ መረጃ ከልቦለድ አንፃር የሚካተቱ ነጥቦችን መመልከት አስፈላጊ ነው።

## 2.2. ረጅም ልቦለድ

ረጅም ልቦለድ በይዘትም ሆነ በሃሳብ ጥንካሬ እንዲሁም በአላባዊያን ትስስርና ጥምረት ሰፋ ያለ ትንታኔ የታሪክ መዋቅርን የያዘ ወጥ የልቦለድ አይነት ነው። በውስጡም በዛ ያሉ ገፀባሕርያት ጠንከር ያለ ትልም ፣ወይም ሴራ የተፈራረቁ መቼቶች ፣ ጠጣር ያለ ጭብጥ፣ውስብስብ ያሉ ሴራዎችን ያካተተ ጠለቅ ያለ የልቦለድ አይነት ነው። ብርሀኑ ገብረፃዲቅ አጠቃላይ የአማረኛ ቋንቋ ረጅም ልቦለድን እንዲህ ሲል ገልፆታል። "ረጅም ልቦለድ በቃላት ያልተገደበ በርከት ያሉ ገፀባሕርያትን እንዲሁም ውስብስብ ሴራዎችን በውስጡ ያካተተ ሰፋ ያለ የልቦለድ አይነት ነው።" (2008፣107)

ዘሪሁን አስፋው የስነፅሁፍ መሰረታዊያን በተሰኘው መፅሃፉ "ረጅም ልቦለድን ረጅም ያሰባሉት ፍሬ ነገሮች ወይም የራሱ አላባዊያን አሉት። እነርሱም ታሪክ፣ትልም (ሴራ)፣መቼት ፣ግጭት ፣ጭብጥ ፣ገፀባሕርያት እና አንፃር ናቸው። እነዚህ ፍሬ ነገሮች ለአጠናን ይመቹ ዘንድ እንጅ በልቦለድ ውስጥ በተናጠል የሚፈረጁ አይደሉም ።" (2005፣ 159)

### 2.2.1. ገፀባሕርያት

ገፀባሕርያት በልቦለዱ ውሰጥ ታሪኩን ይሸከሙልኛል ብሎ የባቤትነት መብት ያወረሳቸው የደራሲው ፍጡሮች ናቸው። ገፀባሕርያት ልክ እንደምናውቃቸው ፍጡራን የራሳቸው የሆነ ስሜት ፣ፍላጎት፣አላማ፣ተስፋና እሳቤ አላቸው።

ዘሪሁን አስፋው የስነፅሁፍ መሰረታዊያን እንዲህ ሲል ገልፆታል። "በአንድ ልቦለድ ውስጥ የሚተረክ ታሪክ የማነው? የሚል ጥያቄ ሲጠየቅ መልሱ በቀጥታ የእነገሌ ታሪክ ነው የሚል ይሆናል። እገሌ ተብለው የሚጠቀሱት ደግሞ የተለያዩ ባህርያትና የህይወት ገፅታዎች ያሏቸው ሰዎች ናቸው። ገፀባህርያት በልቦለድ አለም ስጋ ለብሰው ባህሪ ተጎናፊው መጠርያ ተሰጥቷቸው፣መኖርያ ተበጅቶላቸው፣የሚንቀሳቀሱ፣የሚተነፍሱ፣የሚናገሩ፣ የሚበሉ፣የሚጠጡ፣የሚደሰቱ እና የሚያዝኑ የልቦለድ አለም ሰዎች ናቸው ። ገፀባሕርያት ልቦለዱ ከተፈጠረበት ዘመን የፈለቁ የዚያ ቦታና ዘመን ሰዎች ወኪሎች ሲሆኑ በየዘመኑ የነበረውን አስተሳሰብ እና አጠቃላይ አተያይ ባህልና ማህበራዊ ልማድ፣መንፈሳዊና ቁሳዊ ልማድን ያንፀባርቃሉ።" ዘሪሁን አስፋው (2005፣160)

#### 2.2.1.1. የገፀባርያት አቀራረፅ

የገፀ ባህርያት አቀራረፅ ማለት ደራሲው ገፀባሕርያትን ሲቀርፅ የሚሰጣቸው ባህሪ፣ልማድ፣ስብና፣ስነልቦና፣ አስተሳሰብ፣ተክለ ቁመና፣ልእልና እና የመሳሰሉትን ባህርያት ነው። ለምሳሌ አንካሳ፣ረጅም፣ ውሸታም፣ ሌባ ፣ሰነፍ፣

ትጉህ፣አማኝ፣ኢአማኝ፣ደፋር፣ፈሪ፣ለፍላፊ፣ጋግርታም፣አስታዋሽ፣ዝንጉና የመሳሰሉትን ባህርያት ሲያወርሳቸው የገፀባህርያት አቀራረፅ እንለዋለን ።

ዘሪሁን አስፋው የስነፅሁፍ መሰረታዊያን (2005-160) "ደራሲ ገፀባህርያትን የሚፈጥረው ለህይወትና ለሰው ልጅ ካለው አተያይና አጠቃላይ እውቀት በመነሳት ፤ የራሱን በእውኑ አለም የሚያውቃቸውን ሰዎች አካላዊና ህሌናዊ መልክ ወይም አጠቃላይ ሰብዕና መነሻ በማድረግ ነው።"

## 2.2.1.2. **የገፀባህርያት አቀራረብ ዘዴዎች**

ደራሲው ስለ ገፀባሕርያት ለአንባቢው ለመግቢያ ገለፃ ያክል የሚያትተው ገለፃ እንዲሁም ትውውቅ የገፀባህርያት የአቀራረብ ዘዴ እንለዋለን። ዘሪሁን አስፋው (2005፣167) “የገፀባህርያትን ማንነትና ያሉበትን ሁኔታ ለአንባቢ ለማሳወቅ ደራሲያን የሚጠቀሙባቸው ሁለት አብይት ዘዴዎች አሉ። አንደኛው ርቱዕ ወይም ዘርዛሪ የሚባል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ኢ-ርቱዕ ወይም ተውኔታዊ የአቀራረብ ዘዴ የሚባለው ነው።”

***ሀ, ርቱዕ፦*** “ይህ አቀራረብ ገፀባሕርያቱን በቀጥታ በመግለፅ ወይም በመተንተን የሚያቀርብ ሲሆን ገፀባሕርያቱን ምን እንደሚመስሉ ተራኪው ወይም ዳር ቆሞ የሚታዘብ ገፀባህርይ ይነግረናል። በዚህ አይነቱ ዘዴ አብዛኛው የገፀባህርያቱ አካላዊና ህሌናዊ መልክ በዝርዝር ይገለፃል።” ዘሪሁን አስፋው (2005 :167)

***ለ, ኢ-ርቱዕ (ተውኔታዊ) የአቀራረብ ዘዴ፦*** “ገፀባሪውን በድርጊት ያሳያል። ከገፀባህሪው አመል ፣ንግግር፣አስተሳሰብና አመለካከት፣ሰብእናውንና ከሌሎች ገፀባሕርያት ጋር ያለውን ግንኙነት መገንዘብ ይችላል። በዚህ አይነት የአቀራረብ ዘዴ ደራሲው ገፀባህርያቱን በመድረክ ላይ እንዳለ ተዋንያን እያደረገ እና ድርጊት እያስፈፀመ ስለሚያቀርባቸው አንባቢ መልካቸውን እና ባህርያቸውን ለማወቅ አያዳግተውም።” ዘሪሁን አስፋው (2005፣169)

## 2.2.2. **የገፀባህርያት አይነቶች**

የገፀባህርያት አይነቶች የምንላቸው ብዙውን ጊዜ ደራሲው ገፀባሕርያትን ሲቀርፅ የሚሰጣቸው ትኩረት ወይም የተሰጣቸው አፅኖት ወይም ገረፍታ ነው። ዘሪሁን አስፋው (2005፣171) "የልቦለድ ገፀባሕርያት ፈርጀብዙ እና ፈርጃንድ ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ።"

## 2.2.2.1. **ፈርጀብዙ ገፀባሕርያት**

"ፈርጀ ብዙ ገፀባሕርያት ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተቀረፁ ውስብስብ ባህርይ ያላቸው ገፀባሕርያት ናቸው። እንዲህ ያሉት የልቦለድ አለም ሰዎች በተወሳሰበ የኖሮ ውጣውረድ የተጠመዱ አላማቸውን ከግብ ለማድረስ ሲዋትቱ ብዙ እንቅፋቶች የሚጋረጡባቸው ስለሰው አጠቃላይ ስለህይወት እና ስለተፈጥሮ ሲፈላሰፉ የሚገኙ ከህይወት አያሌ ገፅታዎች ነክነት ያላቸው በቀላሉ የማይታወቁ ገፀባህርያት ናቸው። ፈርጀ ብዙ ገፀባሕርያት በአስተሳሰባቸውም ሆነ በአጠቃላይ ነገረ ስራቸው እንደሚገቡባቸው ሁነቶች እንደሚኖራቸው እርስበርሳዊ ግንኙነት የተለያዩ ባህርያት

*ይታዩባቸዋል። ምኞታቸውን፣አመለካከታቸውን ሙሉ ስብዕናቸውን ለመረዳት ያዳግታል። እንዲህ ያሉት የባህሪ ውስብስብነት የሚታይባቸው ገፀባህርያት በውል ለማወቅ ሰፋ ያለ ትንታኔ ግድ ነዉ ። አስተሳባቸውን ምኞትና ፍላጎቶቻቸውን፣የኖሩበትን ዘመንና አካባቢ እንዲሁም ማህበራዊ ገፅታ ከሌሎች ገፀባህርያት ጋር ያላቸውን ግንኙነት በሚገባ መገንዘብ ያስፈልጋል ። በልቦለድ ውስጥ የሚኖሩ ፈርጀብዙ ገፀባህርያት እንደጤዛ ማለዳ ታይተው ረፋድ ላይ እየጠፉ የሚሄዱ አይደሉም። በብዙዎች ምዕራፍ የሚታዩና በሚፈፅሟቸው ድርጊቶችና የሚገቡባቸው ሁነቶች ዘለግ ላለ ጊዜ የሚቀዩ ሲሆኑ አብዛኛው የልቦለዱ ታሪክ የሚያጠነጥነው በእነሱ ህይወት ዙሪያ ነው።* " *ዘሪሁን አስፋው* (2005፣171)

## 2.2.2.2. *ፈርጃንድ ገፀባሕርያት*

"*ፈርጃንድ ገፀባሕርያት ብቅ ባሉ ቁጥር ወዲያው ሊለዩ የሚችሉ በቀላሉ የሚታወሱ በተደጋጋሚ የሚታይ አንድ የተወሰነ ልማድ ውይም ባህሪ ያላቸው ፣እነዚህ ገፀባሕርያት ከብዙ አቅጣጫዎች ያልተቀረፁ በእውኑ አለም በእለት ተዕለት ህይወት ዘወትር የሚገኙ ሁሉ ሰው የሚያውቃቸው ውስብስብነት የሌላቸውና አብዛኛውን ጊዜ አንድ ወይም ሁለት የታወቀ ባህሪ ያላቸው በአንድ አረፍተነገር ልገለፁ የሚችሉ ናቸው።*

*ፈርጃንድ ገፀባህርያት ሁሌም ይዘውት ብቅ የሚሉት በአንድ ነጠላ ጉዳይ ላይ ያተኮረ ስለሚሆን አንባቢን አያስደንቅም፣ተደጋጋሚ በመሆኑ አሰልች ይሆናል። ገፀባህሪው ብቅ ባለ ቁጥር የመሰልቸት እንጅ ፍላጎቱ ቢሳካለትም ባይሳካለትም አንባቢን ጭንቀት ወይም ሌላ ተመሳሳይ ስሜት ውስጥ በማስገባት በሁኔታው እንዲደመም አያደርግም። ፈርጃንድ ገፀባሕርያት ብዙ ጊዜ የሚፈጠሩት ዋናዎችን ገፀባሕርያት ለማጀብ፣እነሱን ለማጉላት ለአንዳንድ ባህሪያቸው ማንፀባረቂያ ለመሆን ነው።* "*ዘሪሁን አስፋው* (2005፣172)

## 2.2.2. *ግጭት*

*ግጭት ማለት የእያንዳንዱ ገፀባሕርያት የተሰፋ መሰናክል ማለት ነው። ይህም ማለት ገፀባሕርያት የራሳቸው የሆን ምኞት፣ፍላጎትና ስኬት አላቸው። በነዚህ ሁነቶች መካከል የገፀባህርያት አላማን መጣረስ ግጭት እንለዋለን።ብርሃኑ ገብረፃዲቅ* (2008፣108) "*ግጭት አንድ ገፀባህርይ ከሌላው ገፀባህርይ ጋር የሚፈጥረው ንትርክ፣ገፀባሕርያት ይህን ልፈፅም አልፈፅም ብለው የሚፈጥሩት የሃሳብ ቅራኔ ነው።*"

*ዘሪሁን አስፋው* (2005፣172) "*በልቦለድ አለም የሚኖሩ ገፀባህርያት በታሪኩ ውስጥ በተፈጠረላቸው ርስበርሳዊ ግንኙነት የተነሳ በተለያዩ ምክንያቶች ቅራኔዎች ወይም አለመግባባቶች ሳቢያ የሚፈጠረው ፍጭት ወይም ፍልሚያ ግጭት ይባላል ። በሁለት ተፃራሪ ሃይሎች መካከል በሚደረገው ትግል አንዱ ሌላውን ለማሸነፍ፣አንዱ ሌላውን ለመጣል ወይም በሌላው ላይ የበላይነት ለማግኘት ሲጥር ሌላው ላለመሸነፍ ፣ላለመውደቅ ውይም ላለመበለጥ ሲፍጨረጨር ይታያል። በታሪኩ መዋቅር ሂደት የሚከናወኑት ድርጊቶች ግጭት በመሆናቸው ነው ። አንድ ታሪክም*

ወደፊት ሊራመድ የሚችለው ከግጭቱ ውስጥ የሚገቡት አቀንቃኝና ተቀናቃኝ ገፀባህርያት በሚፈፅሟቸው ድርጊቶች ወይም በተፃራሪ ሃይሎች ምክንያት በሚከናወኑ ተግባራት ነው።" (2005-172)

## 2.2.2.1. የግጭት ባህሪያት

የግጭት ባህሪያት በገፀባህሪያት መካከል የሚከሰቱ አለመግባባቶች የሚኖራቸውን ሁነት የሚያጠቃልል ነው። ይህም ማለት ገፀባሕርያት ከሌሎች ገፀባሕርያት ጋር የሚያደርጉት ፍልሚያ ታዓሚኒ ነው ወይ? የግጭቱ መንስዔ በቂ ነው ወይ? ግጭቱ የተፈታበት መንገድስ ምን ይመስላል? የሚለውን ሃሳብ ይይዙልናል።

ዘሪሁን አስፋው (2005፣173-175)" ለልቦለድ የጀርባ አጥንት የሆነው ግጭት እንዲፈጠር ሁለት ተፃራሪ ሃይላት ግጭት ውስጥ ገብተው ድርጊቶችን እንዲፈፅሙ በውል የሚታይ አስገዳጅ ሁኔታ ወይም አላማ መኖር አለበት። ይህ መንስኤ ግጭት የሚታመንና ግጭቱን ለመቀስቀስ ብቃት ያለውና በሰዎች ገጠመኝ ሊከሰት የሚችል መሆን ይኖርበታል። ሌላኛው የግጭት ባህሪ በሁለቱ ተፃራሪ ሃይላት መካከል የሚኖረውን ፍጭት የሚመለከት ነው። አቀንቃኙም ሆነ ተቀናቃኙ ገፀባሕርይ በመንስኤ ግጭቱ የተነሳ ተገደው ግጭቱ ውስጥ ከገቡ በኋላ ለመሸናነፍ ወይም አላማን ለማሳካት ሲታገሉ መታየት አለባቸው። ይህን በሁለቱ መካከል የሚደረግ ፍልሚያ መሆኑ ይታወቃል። እነዚህ ሃይላት ተመጣጣኝ እንዲሆኑ ያስፈልጋል። የልቦለድ ግጭት በሰዎች ገጠመኝ ሊከሰት የሚችልና የሚታመን መሆን ይኖርበታል። በእውኑ አለም ሊያጋጥም የሚችል አይነት ከሆነ ተዓማኒነት ይኖረዋል።''

## 2.2.2.2. የግጭት አይነቶች

*ሀ. __ሰው ከራሱ ጋር__*- ይህ የግጭት አይነት ሰው በራሱ ዛቢያ ሃሳቦችን እያወዳደረ ይመርጣል ። ሆኖም እነዚህ ሀሳቦች ብዙ ጊዜ ተቃራኒ ሀሳቦች ናቸው። ስለዚህ በአንድ ሰው ውስጥ ያሉ ብዙ የማይጣጣሙ ሃሳቦች በህሌናው ውስጥ ውዝግብን ሲፈጥሩ ይህ አይነት ግጭት ይፈጠራል። ለምሳሌ ልግደለው አልግደለው ፣እራሴን ላጥፋ አላጥፋ፣ ልስረቅ አልስረቅ ፣ትዳር ልያዝ አልያዝ የመሳሰሉት ሃሳቦች በሰው ህሌና ላይ ፍልሚያን ያካሂዳሉ ።

ዘሪሁን አስፋው (2005፣175)" ይህ ግጭት ሰው ከራሱ ጋርየሚያደርገው ህሊናዊ ወይም ስነልቦናዊ የሚባለው ግጭት ነው። ይህ አይነት ግጭት በአንድ ሰው ውስጥ በሚኖሩ ፍላጎቶች መካከል የሚፈጠር ቅራኔ ነው።"

***ለ. __ሰው ከሰው ጋር__***- ይህ ግጭት ሰው እንደመልኩ እና እንዳፈጣጠሩ ሃሳቡም እየቅል ነው። ስለሆነም የሰው ልጅ ከሰው ጋር ሲኖር የአንዱ ሃሳብ ካንዱ ሃሳብ ጋር አልጣጣም ሲል እንዲሁም አንዱ የአንዱን ሃሳብ እንዲቀበል አንዱ በአንዱላይ የበላይነቱን ለማሳየት በህይት ውጣ ውረድ ላይ የሚፈጠር ግጭት ነው።

ዘሪሁን አስፋው (2005፣175) "ይህ የግጭት አይነት በሰውና በሰው መካከል የሚፈጠረውና ሰው ከሰው የሚባለው ነው ። ማለትም ሁለት ሰዎች ባላቸው እምነት፣ፍላጎት፣የአላማ ወይም የአቋም እንዲሁም የአስተሳሰብና በስብዕና ልዩነት የሚፈጠር ግጭት ነው።"

*ሐ. <u>ሰው ከተፈጥሮ ክስተቶችና ገፅታዎች ጋር፦</u>* ይህ የግጭት አይነት የሰው ልጅ በተፈጠረለት አለም ውስጥ ሲኖር የራሱን ስሜት ሲከተል ተፈጥሮንና ፈጣሪውን ይጋፋል። ብዙ ተፈጥሯዊ ክስተቶችን ይጋፈጣል። ይህም ግጭት ሰው ከተፈጥሮ ጋር ያለውን ግብግብ ነው የሚገልፀው።

ዘሪሁን አስፋው (2005፣176) "ይህ የግጭት አይነት ሰዎች ለመኖር ሲሉ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎችና ተግባራት ከተፈጥሮ አካላት ጋር ይገናኛሉ። ለምሳሌ ገበሬው ደኑን መንጥሮ የእርሻ መሬት ያዘጋጃል። ይህን በሚያደርግበት ጊዜ ከሜካው ጋር አካላዊ ግጭት የሚፈጥርባቸው ሁኔታዎች ያጋጥሙታል።"

## 2.2.3. መቼት

መቼት ማለት ታሪኩ ተፈጥሮ እስከሚያልቅበት ያለው ጊዜ በተጨማሪም በታሪኩ ውስጥ የተፈጠሩ እያንዳንዱ ሁነቶች የሚከወኑበት ቦታ ማለት ነው። ዘሪሁን አስፋው (2005፣179) "የልቦለድ ገፀባሕርያት እንደ እውን አለም ሰዎች የመኖሪያ አካባቢ አላቸው። በልቦለድ አለማቸው የሚንቀሳቀሱትና ታሪካቸውን የሚፈፅሙበት ደራሲው በመረጠው በተወሰነ አካባቢ ሲሆን የሚኖሩበትና ታሪካቸውን የሚፈፅሙበት ታሪካዊ ጊዜ፣ወቅት፣እለትና ሰዓትም ይኖራቸዋል። ይህ የገፀባሕርያቱ መገኛ ስፍራና ጊዜ ባንድነት መቼት ይባላል።

መቼት ታሪኩ የተከናዎነበትና ገፀባህሪያቱ የሚኖሩበት ወይም የኖሩበት የገጠር ወይም የከተማ አካባቢ አካባቢ ብቻም አይደለም። ከገጠሩ ከከተማው የህይወት እንቅስቃሴ ጋር ያሉትን የተለያዩ ሁኔታዎች አካቶ በመያዙም ጓዘ ብዙ ነው። መቼት በአንድ ጎኑ ታሪኩ የሚፈፀምበት ቦታ ከነጓዙ ሲሆን በሌላ ጎን ደግሞ ታሪኩ የሚፈፀምበት ጊዜ ነው ማለት ይቻላል።"

## 2.2.4. ጭብጥ

ጭብጥ ማለት ደራሲው በገፀባህርያት አማካኝነት ለአንባቢው መንገር የፈለገው አብይ ሃሳብ ማለት ነው። ዘሪሁን አስፋው (2005 ፣185) "ማነኛውም ልቦለድ የሚፃፍበት አይነተኛ አላማ አለው። ይህ አላማው በታሪኩ ሂደት በገፀባህርያቱ ሂደት በገፀባህርያቱ ህይወትና በመካከላቸው ባሉ እርስ በርሳዊ ግንኙነቶች ውስጥ የሚፈስ ሲሆን አንድ አይነት ማህበራዊ ጉዳይ ወይም ቁም ነገር ይዞ የሚነሳ ነው። ደራሲው የግል ገጠመኙን ለማህበረሰቡ ልዩ ልዩ ገፅታዎች ያለውን አመለካከትና እውቀት መሠረት በማድረግ በልቦለዱ ውስጥ የሚቀረፀው አብይ አላማ የልቦለዱን አያሌ ፈርጆች አስተሳስሮ ይይዛል።

ጭብጥ ምንግዜም ሰዋዊ ቢሆን ይመረጣል። የሰውን መሰረታዊ ባህርያት የሚያንፀባርቅ ሰዉ ከተፈጥሮና ከማህበራዊ አካባቢው ያለውን ግንኙነት የሚነካ የሰው ልጅን የአኗኗር ስርዓት ለመኖር ሲል የሚፈጥራቸውን አይቀሬ ግንኙነቶች የሚጠቅስ ሲሆን ሰዋዊነቱም የጎላ ይሆናል። አንዳንድ ሃያሲያን የአንድን ልቦለድ ትልቅነት የሚመዝኑት በጭብጡ ሰዋዊ መሆን ነዉ። የአንድ ልቦለድ አብይ ጭብጥ የሰዎችን የጋራ ባህርያትና የጋራ ገጠመኞችን ያሳየ እንደሆነ ሁለንተናዊነት አለው ይባላል። ሆኖም የልቦለድን ጭብጥ ለማግኘት ወይም ይሄ ነው ብሎ በቀጥታ ለመናገር

ቀላል አይደለም። ጥልቅ ምርምርንና የተወሳሰቡ ነገሮችን ፈትቶ የማየትን ችሎታ የሚጠይቅ ተግባር ነው።" ዘሪሁን አስፋው (2005፣185)

## 2.2.5. ታሪክ

ታሪክ ማለት የደራሲው የተቀናጀ የክንዋኔዎች ቅደም ተከተል ወይም የልቦለዱ ንድፍ ነው። ታሪክ ቀድሞ ከአንባቢው ህሊና የሚገባ የገፀባህርያት ድርጊት ስርዓት ነው። ዘሪሁን አስፋው (2005፣155-157) "ታሪክ በልቦለድ ቀዳሚው ነገር ነው። የልቦለድ መሰረታዊ ገፅታ አንድ አይነት ታሪክ መተረኩ ነው። ታሪክ በተወሰነ የጊዜ ቅደም ተከተል የተቀናጁ ሁነቶች ትረካ ነው። ደራሲው በታሪኩ ውስጥ የተለያዩ ሁነቶችን ያበጃል። በሁነቶችም ሰንሰለታዊ ጉዞ ታሪኩ ከአንዱ ደረጃ ወደ ሌላው ሲተላለፍ ባለታሪኮች የተለያዩ ድረጊቶችን በመፈፀም ማንነታቸውንና የሚደርስባቸው ክፉም ሆነ ደግ ነገር ይታያል። በልቦለድ ታሪክ ሰፋት እያገኘ የሚሄደው ገፀባህሪያት የየራሳቸው ባህሪ አመለካከትና አስተሳሰብ ሲኖራቸውና ተራኪው ይህን ሁሉ በመተረክ የርስበርስ ግንኙነታቸውን መሰረትና ግንኙነት ሲያሳይ ነው።''

## 2.2.6 ትልም

ትልም ማለት የእያንዳንዱ የታሪክ ሁነት ሰበበ ድርጊት እና ምክንያት እንዲሁም ምክንያቱ ይዞት የሚመጣው ውጤት ነው። ደራሲው ትልሙን በሚያዋቅርበት ጊዜ ለእያንዳንዱ መንስኤ ብቁ የሆነ ውጤት እንዲሁም ለውጤቱ መፈጠር ተዓማኒ የሆነ መንስኤ ከተለመ ብቁ የሆነ ትልም ይሆናል።

ዘሪሁን አስፋው (2005፣158) "ትልም በአንድ ልቦለድ ውስጥ ምን? ለምን ተደረገ? ብለን ስንጠይቅ የምናገኘውን መልስ የሚያካትት ወይም በጊዜ ቅደም ተከተል የተፈፀሙ ሁነቶች የተደረጉበትን ምክንያትና የሚያስከትሉትን ውጤት ጥብቅ ቁርኝት የያዘ የልቦለዱ አካል ሲሆን ፣ታሪክ ደግሞ ምን ተደረገ ከዛስ ቀጥሎ ምን ሆነ ስንል የምናገኘው ምላሽ ነው። ትልም ሊባል ሚችለው ሁነቶች በምክንያትና ውጤት ግንኙነት በውል ተቀናጅተው አንድ አይነት ሁባሬ የፈጠሩ እንደሆነ ነው። የአንድ ልቦለድ ትልም መሠረት አቀንቃኙ/ኟ ገፀባህርይ የሚፈፅሟቸው ድርጊቶችና የደራሲው ዋነኛ አላማዎች ናቸው። ስለዚህ የገፀባህሪያቱ ሰብእናና ስነልቦናዊ መልክ የሚገቡባቸው ሁነቶችና ከማህበራዊ አካባቢያቸው ጋር ባለው ግንኙነት ምክንያት የሚፈፅሟቸው ዋና ዋና ድርጊቶች እንዲሁም ልቦለዱ ያቀፈው ማዕከላዊ አላማ በአንድ ተጣምረው ትልሙን ይመሰርታሉ።''

## 2.2.6. አንፃር

አንፃር ማለት ደራሲው ታሪኩ እነዲተረክለት የፈለገው አቅጣጫ ወይም ታሪኩን እንዲነግርለት የመረጠው የታሪኩ መልክተኛ የሚያቀርብበት መንገድ ነው። ዘሪሁን አስፋው (2005፣190-191) "ማነኛውም ልቦለድ በደራሲውና በአንባቢው መካከል ሆኖ ሁነቶችን የሚገልፅና የሚተረጉም አልፎ አልፎም በግልፅ አብዛኛውን ጊዜ ግን

በውስጥ ታዋቂ የሚኖር የታሪኩን ሂደት እየተከታተለ የሚያቀርብ ተራኪ አለው። ተራኪው ታሪኩ የሚመለከተው ተሳታፊ ወይም ታሪኩ የማይመለከተው ታዛቢ ሊሆን ይችላል። ተሳታፊ ከሆነ ታሪኩ የሱም ታሪክ በመሆኑ የራሱንም ሆነ ከሱጋራ ግንኙነት ያላቸውን ገፀባሕርያት ታሪክ በሱው አመለካከት ያቀርባል። ታዛቢ ከሆነ ደግሞ ቀሞ ያየውንና የታዘበውን እንዳለ ነው የሚያቀርበው። ስለዚህ ታሪኩን የሚተርከው ማነው? ከታሪኩስ ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነው? ታሪኩ የተተረከው ከማን አኳያ ነው? ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥና ደራሲው የልቦለዱን ታሪክ የሚያቀርብበት የትረካ አቅጣጫ ነው። ደራሲያን የልቦለዳቸውን ታሪክ የሚያቀርቡባቸው አራት መሰረታዊ የአንፃር አይነቶች አሉ። እነርሱም ሁሉን አወቅ አንፃር፣ውስን ሁሉን አወቅ፣አንደኛ መደብ እና ተውኔታዊ አንፃር ተብለው ይጠራሉ።" ዘሪሁን አስፋው (2005፣191)

## 2.2.6.1. ሁሉን አወቅ አንፃር

ይህ የአንፃር አይነት ተራኪው የገፀባህሪያትን ስነልቦና እና እሳቤ በሚገባ ስለሚያውቅ እያንዳንዱን ሁነት በዝርዝር ለአንባቢ ይነግራል። ዘሪሁን አስፋው (2005፣191) "ይህ አንፃር ለተራኪው ሰፊ ነፃነት የሚሰጥና በሦስተኛ መደብ የሚተረክ የትረካ አንፃር ነው። ቃሉ እንደሚያመለክተው ተራኪው በልቦለዱ ውስጥ የሚከናዎነውን ሁሉ የገፀባህሪያቱን ማንነት፣ስሜትና ሃሳብ፣ምኞት እና ፍላጎት በሚገባ ያውቃል። ይህ አንፃር አንዳንድ ችግሮች አሉት። ከነዚህም መካከል ዋነኛው አንድም ሳያስቀር ዘክዝኮ ስለሚያቅርብ አንባቢያን እንዲመራመሩና የገፀባህሪያቱን ማንነት ከድርጊታቸው ለማወቅ እንዲችሉ እድል አለመስጠቱ ነው።"

## 2.2.6.2. ውስን ሁሉን አዎቅ አንፃር

ውስን ሁሉን አወቅ አንፃር ተራኪው ልክ እንደ ገፀባህርያት የታሪኩን ግንባር ለማወቅ የተገደበ ነው። ሁነቱን የሚመለከተው ልክ ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ አሊያም ዘግይቶ ነው። ያም ሆኖ አንባቢውን የመፈለግ እና የመገመት እድሉን በተሻለ መንገድ ያሳድግለታል።

ዘሪሁን አስፋው (2005፣194)" ውስን ሁሉን እወቅ አንፃር እንደ ሁሉን አወቅ አንፃር በሶስተኛ መደብ የሚተረክ ሲሆን ተራኪው የሁሉንም ገፀባህርያት ስሜት አስተሳሰብም ሆነ ፍላጎት አያውቅም። የራሱንም ፍልስፍናና አስተያየት የመንዛት አቅሙ የተገደበ ነው። ውስን ሁሉን አወቅ አንፃር ገፀባህርያትን ከአንባቢ በማቀራረብ ረገድ ከሁሉን አወቅ የተሻለ ነው። የሚያስከትለው ችግር ደግሞ የተመረጠው ገፀባህርይ የሚያቀርበውን ከመከታተል አንባቢው አልፎ ስለማይሄድና የገፀባህሪውም እውቀት የተገደበ ሊሆን ስለሚችል አንዳንድ አስፈላጊ ነገሮችን አንባቢው ሊያጣ ይችላል።

## 2.2.6.3. አንደኛ መደብ አንፃር

አንደኛ መደብ አንፃር አንድ የሆነ ገፀባህሪ የልቦለዱን ጉዞት ከራሱ አንፃር እየተረከ በራሱላይ የሆነበትንና በሌሎችም ገፀባህርያት የተፈፀመውን ድርጊት ለአንባቢ ያቀርባል።

ዘሪሁን አስፋው (2005፣197) "ተራኪው እኔ ይህን አየሁ ፣ይህን ተመለከትኩ ፣እገሌ የተባለው ገፀባህርይ በዚህ ወጣ፣ በዚህ ወረደ ፣ እገሌ ደግሞ እንዲህ ያለ ችግር ደረሰበት፣ በራሴ ላይ እንዲህ ያለ ድርጊት ተፈፀመብኝ እያለ የሚተርክበት የአንፃር አይነት ነው። እኔ ባዩ እንደታሪኩ ሁኔታና እንደደራሲው ምርጫ የልቦለዱ አብይ ወይም ንዑስ ገፀባህርይ ሊሆን ይችላል ።"

## 2.2.6.4. ተውኔታዊ አንፃር

ተውኔታዊ አንፃር አንባቢው ልቦለዱን በሚያነብበት ወቅት ገፀባሕርያት በሚያደርጉት ሁነት ፣ የአሰተሳሰብ ዝንባሌ፣ በሚያወሩት ወሬ፣ለሁነቱ ባላቸው ምላሽ ወይም አቀባበል ገፀባህሪያትን በውስጡ የሚዳኝበት መንገድ ነው።ዘሪሁን አስፋው (2005፣200) "ተውኔታዊ አንፃር ተራኪው በገፀባህሪያቱ ድርጊትም ሆነ በሁነቶች ምንም አይነት አስተያየት የማይሰጥበት የአንፃር አይነት ነው። በታሪኩ ውስጥ የሚከናወኑ ድርጊቶችም ሆነ የገፀባህርያት ግኙኝነቶች ወይም የሚገቡባቸው ሁኔታዎች እንዳሉ ነው የሚቀርቡት። ይህ አንፃር አንባቢው በራሱ ምልከታ ገፀባህሪያትን ከንግግራቸው ገምግሞ የራሱን ፍርድ የሚሰጥበት ነው። የተራኪው ተግባር ፊትለፊቱ የተደቀነውንና የሚታየውን የራሱን ስሜት ሳይጨምር እንዳለ መቅረፅ "ካሜራዊ አቀራረብ " እየተባለ ይጠራል። በዚህ ባህሪዉ ጠቃሚነት ሲኖረው ተራኪው በመሀል ገብቶ አንዳንድ ሁኔታዎችን ስለማያብራራ አንዳንድ አንባቢያን ታሪኩን ለመረዳት ይቸገሩ ይሆናል።"

## 2.3. የተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፍ ቅኝት

መላኩ ተሰፋ 2012 "ግራጫ ቃጭሎች ረጅም ልቦለድ ከገፀባህርያት አሳሳል አንፃር" ጅማ ዩኒቨርሲቲ ። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ለበችለር አርትስ ዲግሪ ማሚያነት የቀረበ ሲሆን ግራጫ ቃጭሎች ረጅም ልቦለድን ከገፀባህሪ አሳሳል አንፃር ይተነትናል። ጥናታዊ ፅሁፉ አጥኚው ከሚያጠናው ጥናት ጋር አንድነትም ልዩነትም ያለው ሲሆን፣ አንድነቱ ሁለቱም ጥናቶች ስለገፀባህርያት በቂ ትንታኔ ለማቅረብ ሞክረዋል። ከነዚህም መካከል "ግራጫ ቃጭሎች ረጅም ልቦለድ ከገፀባህርያት አቀራረብ፣ከገፀባህርያት አቀራረፅ እንዲሁም ፣ከገፀባህርያት አይነቶች አንፃር የዳሰሰ ሲሆን አጥኚውም እነዚህን ሃሳቦች በጥናቱ ውስጥ ለማካተት ሞክሯል። ጥናቱ አጥኚው ከሚያጠናው ጥናት የሚለየው ደግሞ ይህ ጥናት ቴሎስ ረጅም ልቦለድን ከሰባቱ የልቦለድ አላባዊያን አንፃር የተሰራ በመሆኑ ሰፋ ያለ ሃሳብን ስለሚያጠቃልል ነው።

ሌላኛው እንደ ተዛማጅ ፅሁፍ ብሎ አጥኚው የተመለከተው ጥናት ሰብለወርቅ አጉማሴ 2013 "ተልሚድ ረጅም ልቦለድ ከልቦለድ አላባዊያን አንፃር" ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ። ይህም ጥናታዊ ፅሁፍ ለባችለር አርትስ ዲግሪ ማሚያነት የቀረበ ሲሆን ሁለቱም ከልቦለድ አላባዊያን አንፃር የተሰራ ይሁን እንጅ ጥናቱ አንድነትም ልዩነትም ይታይበታል። ጥናታዊ ፅሁፉ አጥኚው ከሚያጠናው ፅሁፍ ጋር ያለው አንድነት ሁለቱም ስለርዕሰጉዳዩ ግንዛቤ መስጠት ሞክሯል ። ማለትም ሰብለወርቅ ባጠናችው ጥናት ውስጥ ስለልቦለድ አላባዊያን ትንታኔ እና ተልሚድ

ረጅም ልቦለድን ከአላባዊያን አንፃር ለመተንተን ሞክራለች። አጥኚው የሚያጠናውም ይህን ርዕሰ ጉዳይ ለመተንተን ሞክሯል። ልዩነቱ ደግሞ የሁለቱም ልቦለዶች ልዩነት እንዳለ ሆኖ አጥኚው ተጨማሪ የልቦለዱን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ለመዳሰስ ሞክሯል።

ሶስተኛው አጥኚው ለተዛማጅ ፅሁፍ የመረጠው ጥናት ወንድወሰን ሙሉጌታ በ2001 "የዋና ገፀባህርይ አሳሳል በአውሎንፋስ ዳንኪረኞች ረጅም ልቦለድ ውስጥ" ለቋንቋዎች ጥናት ተቋም አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ። ይህም ጥናት በተመሳሳይ ለባችለር አርትስ ዲግሪ ማሟያ የተሰራ ጥናት ሲሆን አጥኚው ከሚያጠናው ጥናት ጋር አንድነትና ልዩነት አለው። አንድነቱ ወንድወሰን በጥናቱ ውስጥ ስለልቦለድ ፣ስለረጅም ልቦለድ፣ስለገፀባህርያት፣ስለገፀባህርያት አቀራረፅ፣ ስለገፀባህርያት አቀራረብ፣እንዲሁም በአውሎ ንፋስ ዳንኪረኞች ረጅም ልቦለድ ውስጥ የዋና ገፀባህሪውን ህሌናዊና አካላዊ አቀራረቦችን እንደዳሰሰ ሁሉ አጥኚውም እነዚህን ርዕሰ ጉዳዮች በርከት ባሉ ገፀባህርያት ለመተንተን ሞክሯል። ልዩነቱም ወንድወሰን ያጠናው ጥናት በአንድ ገፀባህሪ ብቻ የተወሰነ ሲሆን አጥኚው የሚያጠናው ጥናት ግን ቴሎስ ረጅም ልቦለድን ከልቦለድ አላባዊያን አንፃርና ጠንካራና ደካማ ጎኑን ከአላባዊን አንፃር ምክኒያታዊ በሆነ መልኩ ለመተንተን ሞክሯል።

## ምዕራፍ ሶስት

## 3. የመረጃ ትንተና

### 3.1. የቴሎስ ረጅም ልቦለድ ጭምቅ ታሪክ

ያሬድ አባቱ መምህሬ በጎንደር የሚገኘውን ለሌሎች ሚስጥር የሆነውን የጥበብ ሚስጥር እንዲፈልግ ስለነገረው ያንን ጥበብ ከግብ ለማድረስ የሚያፈቅራትን ሚስቱን ጥሎ ከጎንደር ወደ አዲስ አበባ ተሰደደ። ብርቄም ባሏን ያሬድን ለመፈለግ ከጎንደር አዲስ አበባ እንዲሁም ሌሎችም ከተሞች በማሰስ ላይ ሳለች ፅንሷ ገፍቶ ወንድ ልጅ ተገላገለች። ወርቄ አራስነቷን በወጉ ሳታበቃ ልጇን ከተከራየችበት ቤት ጥላ ያሬድን ፍለጋ ወደ አዲስ አበባ ተሰደደች። ከቀናት በኋላ ወደ ጎንደር ተመልሳ ልጇን ለማግኘት ስትሞክር አከራዮች ለ ሲአይኤ (CIA) ማሳደጊያ ተቋም አስረክበውት ቆዩ። ወደ ድርጅቱም ሄዳ ልጁን ለማግኘት ስትሞክር አንድ ፈረንጅ ልጁን ለማሳደግ ውጭ እንደወሰደው ሰማች። በመቀጠልም አንድ መስፍን የሚባል በኢትዮጵያ፣ አሜሪካ እና ሌሎችም ሃገራት የእፅ ዝውውር እንዲሁም በሽብር ጥቃት የሚጠረጠር በተጨማሪም አንድ የአሜሪካ የምርምር ተቋም በሱላይ የመከታተያ መሳሪያ ተገጥሞለት የምርምሩ ሙከራ መተግበሪያ ለማድረግ በክትትል ላይ ሳለ በክትትሉም ሂደት በሱ በኩል የምርምሩ ስራ ስኬታማ እየሆነ አደለም በማለት ማደጎ ቤት ያመጡትን የወርቄን ልጅ የመስፍን ልጅ ነው ብለው በማሰብ ህፃኑን ለምርምሩ ማስቀጠያ በአሜሪካ ሰላዮች ተሰረቀ። ሆኖም ልጅ መውለድ ስላልቻሉ በልጅ ምትክ ከማደጎ ቤት አንድ ልጅ አምጥቶ ለማሳደግ ቢሞክርም ሳይሳካላቸው የትዳር ሁኔታው ፈረሶ አለም በቃኝ ብሎ ወደ ደብረ ዳሞ ገዳም ገባ። ለሁነቱ ምሳሌ ስንመለከት ከስር በተጠቀሰው ገፅ "ልጄ መስፍን ዛሬ ማታ በቅርብ ለገባችሁ ልጆች ትምህርት ስለምሰጥ ከገዳሙ እንዳትቀር።" (ቴሎስ ገፅ 94)

በነዚህ ሁነቶች መካከል አንድ አሊሰን የምትባል እጅግ በጣም ትጉህ የአሜሪካ ሰላይ ለአንዳንድ ተልኮዎች ወደ ምስራቅ አፍሪካ ሱዳንና ኢትዮጲያ ትመጣለች ። ብዙ ጊዜም መስፍንን ስትከታተል ስለነበር። የመስፍን ልጅ ያለበትን ስለምታቅ ወደ ገዳሙ ሄዳ የልጁን ፎቶ አሳይታ ከመስፍን መወዳጀት ጀመረች። የታቤል (የመስፍን ልጅ) አሳዳጊ ሊንዳ ግን ከኢትዮጲያ አሜሪካ ኮሎራዶ ስቴት ዩኒቨርስቲ ትምህርቷን ጨርሳ ዩንቨርስቲው ሁለተኛ ዲግሪዋን ከዛዉ እንድትቀጥል እድል ተሰጥቷት በአሜሪካ መንግስት በኩል ታቤልን ማንነቱን ደብቃ እናት ሆና እንድታሳድገው ትዕዛዝ ተሰጥቷት አሳድጋ ለቁም ነገር አብቅታዋለች። ታቤልም በአንድ የኮሎራዶ ስቴት ትልቅ የምርምር ተቋም ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ተመራማሪ ሆኗል። አሊሰንም ከጊዚያት በኋላ ከምትሰራበት የስለላ ድርጅት ውጭ አንድ መረጃ ሰማች። ይህ መረጃ በነታቤል የምርምር ተቋም መንትዮሽ ህንፃ ላይ ቀጣይ መስከረም 1/01/1994 ዓም አሸባሪወች ጥቃት እንደሚፈፅሙ ነበር። አሊሰን ይህን ሚስጥር ለሊንዳ ነግራ ታቤልን ለማስመለጥ ትጥራለች። "ትልቅ የሽብር ቡድን በነታቤል ህንፃ ላይ አደጋ ሊጥል እንደሆነ መረጃ ደርሶኛል።" (ቴሎስ ገፅ169)

ያሬድና መሸሻም በሽብሩ እለት የሚሎሪናን የክታብ ሚስጥር ለማስፈታት በኮሎራዶ ስቴት መንትዮሽ ህንፃ ላይ ቀጠሮ ይዘው ከነታቤል ጋር ተገናኙ ። ውይይቱ ሳይጀመር የኮሎራዶ መንትዮሽ ህንፃ በአውሮፕላን መደብደብ

ጀመረ። በዚህ ጊዜ ታቤልን ጭንብል የለበሱ ሰዎች በመኪና አፍነው ሌላ እሱን መሳይ ሰው በሰርጀሪ በማሰራት ቢሮው በማስገባት ይዘውት ጠፉ። ያሬድ የእፀ- መሰዉሩን ድግምት በማነብነብ ከኢትዮጲያ የተሰረቁ የጠልሰም ሚስጥራዊ ስዕሎች እንዲሁም ፅሁፎችን በመያዝ ሊንዳን እና መሸሻን ይዟቸው ወደነ መሸሻ ቤት ተሰወረ።"ያሬድ የማወራህ አለኝ ። ቀይ እንዴት ተርፈን እዚሁ ልንመጣ ቻልን?" (ቴሎስ ገፅ 190) ያሬድ ወደ መሸሻ ቤት ሲገቡ ድንገት አንድ አስገራሚ ነገር አየ። አገኛታለሁ ብሎ ያላሰባትን ብርቄን ከመሸሻ በራፍ ቆማ ተመለከታትና በሃፍረት ከግድ ተደፋ። " ተወኝ ዝም ብለህ ያሬድ እንዳገኘሽኝ አትቁጠረው፤ የተበላሸ ህይወት ነው ያገኘሽው።ህይወቴ ተበላሽቶ የቀረው ደግሞ ባንተ ምክንያት ነው። (ቴሎስ ገፅ 184) ከዚያም ከብዙ ወቀሳና ውይይት በኋላ እራሳቸውን ተቃቅፈው አገኙት። አሊሰን ታቤል ታግቶ ለብዙ ጊዜ ሳያወራ ቢቀይም በአንድ ጀልባ ውስጥ ሀገር በማቋረጥላይ ሳሉ ሁሉንም ያለፈ ታሪኩ ነግራ ኢትዮጵያ ውስጥ ታላቅ የምርምር ተቋም እንደተሰራና የጀመረውን ጥናት ሊጨርስ እንደሚችል ነገረችው። " ታቤል አሁን ማተኮር ያለብህ የጀመርከው ጥናት ላይ ነው በመጨረሻ ይዘኸው የነበረውን የጥናት ውጤት አብረን ስላመጣነው በምትሄድበት ቦታ ትቀጥለዋለህ። ከአሜሪካ የሚበልጥ የምርምር ተቋም ተገንብቶልሃል።" (ቴሎስ ገፅ 200) ከቀናት በኋላም ሁሉም ሌላ እስቴት የነበሩ ኢትዮጵያንን በማሰባሰብ ደብረ ዳሞ ገዳም ከአባ ላዕከ ማርያም ዘንድ ቀርበው የሚሎሪናን ሚስጥር ለማስፈታት ተገናኙ።

## 3.2. ቴሎስ ረጅም ልቦለድ ከትልም አንፃር

ያሬድ አባቱ የሰጠውን የአደራ ሚስጥር ለመፍታት ወርቄን ጥሎ ከጎንደር አዲስ አበባ ለፍለጋ ጠፉ። ወርቄም ያሬድን ለመፈለግ ልጇን ጥላ ጠፋች ። ለመፈለግ በሄደችበትም ጊዜ ልጇን ለሌላ አሳዳጊ ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የመስፍንን ቤተሰብ ለማፅናናት ከ ሲአይኤ ስራ አስኪያጅ ጋር ወዳጅ ስለነበሩ ለመስፍን ስለተሰጠ ከሃገር ውጭ ለአሳዳጊዎች ተሰጥቷል በማለት ወርቄን ከሃገር እንድትወጣ በቃች። መስፍንም ልጁን በመሰረቁ ብዙ የህይወት መስመሩ ተቀየረ ። ከሚስቱ ከትርሲት መለየቱ እንዲሁም የመጠጥ አመሉ የጀመረው እና አለም በቃኝ ብሎ ወደገዳም የገባባቸው ምክንያቶች ሁሉ የልጁ መጥፋት አይነተኛ መንስኤ ሆኖታል። ከጊዚያት በኋላ አሊሰን ባሳየችው ተከታታይ ውጤታማ የሰለላ ተግባር ለምስራቅ አፍሪካ ተልኮዎች ወደ ሱዳን እንዲሁም ኢትዮጵያ ትዕዛዝ ተሰጣት። "ለሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታት በሱዳን ካለው የአሜሪካ ኤምባሲ ሰራተኛ ጋር በመሆን ከአሸባሪዎች ጋር ግንኙነት አለው ተብሎ የተጠረጠረ አንድ አሜሪካዊ ኢንቨስተር ትከታተያለሽ" (ቴሎስ ገፅ 46) ይህ ትዕዛዝ በተሰጣት ወቅት ማንነታቸው ያልታወቁ ሰላዮች ጎን ለጎን እናትሽን እና ልጅሽን ማዳን ከፈለግሽ የኛንም በግል የምንሰጥሽን ትዕዛዝ ትፈፅሚያለሽ የሚል ደብዳቤ በተደጋጋሚ ከበሯ ስር እየጣሉ የተለያዩ ትዕዛዞች ይሰጧት ነበር። የመጀመሪያው ትዕዛዝ ከመስፍን የቀበረችውን መከታተያ ማውጣት እንዲሁም ከመስፍን ጋር ተግባብታ ከአሜሪካ ደህንነቶች ጋር የሰረቀችውን የመስፍን ልጅ ለማስመለስ እንድትሰራ በናቷና በልጇ ህይወት በኩል ሲመጡባት ሁሉንም ተግባራት በስርዓት ለመፈፀም ተስማማች። ሊንዳም የታቤል እናት እንደሆነችና ሚልተንን አባትህ ነው ብላ ማንነቱን ደብቃ እንድታሳድግ ትዕዛዝ ስለተሰጣት ታቤል ለዘመናት ያህል ማንነቱን ሳያውቅ ኖሯል። ታቤል በኮሎራዶ በተጣለው አደጋ ኢትዮጵያዊ በሆኑ ደህንነቶች ህይወቱ ሲተርፍ ሌሎቹ ባልደረቦቹ እንደ እነ ሚልተንና ሎረንስ የመሳሰሉት

የምርምሩ አካላት በስብሰባ መሃል ህይወታቸው አልፏል። ከብዙ ድካም በኋላ ያሬድም የአባቱን አደራ የሚሎሪና ክታብ ትርጉም 33 ዓመት ቢፈጅበትም ለአላማው የከፈለው መስዋዕት ልፋቱን ለፍሬ አብቅቶታል። አላማውም ከግብ በመድረሱ ለኢትዮጵያዊያኖች የተሰፋ ቃል አወጀ ። ምሳሌ ከስር በተጠቀሰው ገፅ የተባለውን መቃኘት ይቻላል። " ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ ጊዜው የኢትዮጵያ ነው።" (ቴሎስገፅ 194) ያሬድ ለሃገሩ የከፈለው መስዋዕት የፍቅሩን እድሜ አልመለሰለትም። የነበራቸው ፍቅር እውነተኛም ሆኖ ከብዙ በደል በኋላ ይቅርታ ቢባባሉም የፍቅር ህይዎታቸው በአጭር ቀጭቶታል። "ወርቅዬ እንኳን ፈጣሪ አገናኘን እንጅ ሁሉንም ነገር እኔ አስተካክለዋለሁ።" ወርቄም በዚሁ ገፅላይ "አይ ያሬድ ከዚህ በኋላ እርጅናችንንና ሞታችንን እንጠብቃለን እንጅ ምን የሚስተካከል ነገር አለ?" (ቴሎስ ገፅ 188)

የቴሎስ ረጅም ልቦለድ ሴራ ትውስብ የበዛበትና ለዋናው ሴራ ሌላ በርከት ያሉ ኢጋዥ ሴራዎችን ያዋቀረ የአፈታቱም ሆነ የሴራው አገነባብ ታማኝ የሚባል አይነት ነው። ምሳሌ ለመውሰድ ያህል የያሬድ መጥፋት ለልጃቸው መጥፋት የልጃቸው መሰረቅ ለወርቄ መሰደድ እንዲሁም ለመስፍን ገዳም መመነን ከዛም የልጁ መጥፋት ድጋሚ ከወርቄ ጋር ለመገናኘት እንዲሁም የታሰበው የሚሎሪና ክታብ ፍች ለአላማ እንዲደርስ እያንዳንዳቸው የሴራ ጥምረት ለሁነቶች መንስኤ እየሆኑ ታሪኩን በጥሩ ወደፊት አስጉዘውታል።

## 3.3. ገፀ-ባህርያት በቴሎስ ረጅም ልቦለድ

በቴሎስ ልቦለድ ውስጥ ገፀ-ባህርያት የቀረቡበት መንገድ በአብዛኛውን ወደ ተውኔታዊ የአቀራረብ ዘዴ ያመዘነ ነው። ይህም ማለት በምዕራፍ ሁለት እንደቀረበው የገፀባህሪያትን ማንነት ለማዎቅ በሚያወሩትና በሚያደርጉት እንጅ አልፎ አልፎ ካንዳንድ ገፀባህርያት በቀር የገፀ-ባህርያት አካላዊ አሳሳል በልቦለዱ ውስጥ ሙሉ በሙሉም ሊባል በሚችል ሁኔታ በአብዛኛው አልተገለፀም ለማለት ያስችላል። ሆኖም የዋና ገፀ-ባህርያትን አቀራረብ ስንመልከት…

### 3.3.1. የያሬድ የገፀ-ባህሪ አሳሳል በቴሎስ ረጅም ልቦለድ

ያሬድ አባቱ የሚሎሪናን ሚስጥር አደራ በሰጠው ጊዜ ገና በሃያዎቹ እድሜላይ ያለ ወጣት ነበር። ሆኖም ሚስጥሩን ለመፈለግ የፈጀበትን እድሜ 33 ዓመት ስንደምርበት ከ 55 - 60 የዕድሜ ክልል ውስጥ ያለ ጎልማሳ ነው። ያሬድ ወርቄን አግብቶ አንድ ልጅ የወለደ እና የመሰወር ጥበብ ባለቤት ለአላማው አቋሙ ዘባ የማይል እና ላሰበው ጉዳይ ወደ ኋላ የማይል መንፈሰ ብርቱና አፍቃሪ ሆኖ በልቦለዱ ውስጥ ተስሏል።

### 3.3.2. የወርቄ የገፀ - ባህሪ አሳሳል በቴሎስ ረጅም ልቦለድ

ወርቄ መልከ መልካም እንዲሁም አመለ ሰናይ እና ፅኑ አፍቃሪ ስትሆን ከያሬድ አንድ ወንድ ልጅ የወለደች ለባሏ እስከ መጨረሻው የታመነች ሴት ነች። ለምሳሌ ያህል በሌላ ገፀባህርይ ስለወርቄ የተገለፀውን መቃኘት ይቻላል። "ያኔ ቤቱን ስትከራይና አሁን ያለቻት ወርቄ ሰማይና ምድር ናቸው። ያኔ ስትመጣ እንደስሟ ወርቅ የምትመስል ችግር በአጠገቧ አልፎ የማያውቅ ልጅ ነበር የምትመስለው። (ቴሎስ ገፅ 26) ወርቄ ቅን ልቦና ያላት ስታፈቅር ምላሽ የማትጠብቅ አደራዋን የምትጠብቅ ትጉህ ሴት ተደርጋ ተስላለች።

### 3.3.3. የመስፍን የገፀ - ባህሪ አሳሳል በቴሎስ ረጅም ልቦለድ

መስፍን እድሜው የጎልማሳ የማይባል ገፋ ያለ እድሜ ያለው፡፡ ነገር ግን እሱ የርጅና ድካም ያልነካካው ብርቱ ሰው ነው፡፡ ምሳሌ ለመመልከት ያክል " ያሬድ ካባ የለበሰውን ሰው አይቶ በድንጋጤ መስፍን! አለው እገዳሙ ውስጥ ብዙ ጊዜ አብረው ያሳለፉ ቢሆንም መስፍን ግን ምንም አይነት እርጅና አይታይበትም ነበር፡፡" (ቴሎስ ገፅ-137) መስፍን ከመነኮሰ በኋላ ራሱ ላይ ቀብ የሚያዘወትር ሸበጥ እንዲሁም ቢጫ ልብስ እንደሚያዘወትር ይገልፃል፡፡ "ከራሱ ላይ የደፋው ቀብ ያገለደመው ቢጫ ነጠላና የተጫማው ሸበጥ ፍፁም መነኩሴ አስመስሎታል፡፡ መስፍን ባሰበው ነገር ቀራጥ በሃገሩ ሰው የተከበረ ነው፡፡ የትዳር ሁኔታው ትርሲት የምትባል ሴት አግብቶ ነገር ግን ልጅ መውለድ የማይችል በዚህም ሳቢያ የተቃቃረ ትዳር የነበረው ትዳሩ አልሳካለት ሲል ወደ ገዳም የገባ ሰው ነው፡፡ መስፍን ከሁሉም በላይ ለልጅ ፍቅር ያለው ህይወት አልሆን ባለም ጊዜ ጠጭ፣ሱሰኛ እንዲሁም አደንዛዥ እፅ ተጠቃሚ ሆኖ ሁሉንም ህይወት የቃኘ በመጨረሻም ጊዜ በገዳሙ ጥሩ ቦታ የሚሰጠው አበምኔት ሆኗል፡፡

### 3.3.4. የአባ ላዕከ ማርያም የገፀ-ባህሪ አሳሳል በቴሎስ ረጅም ልቦለድ

አባ ላዕከ ማርያም በደብረ ዳሞ ገዳም ውስጥ ልዩ ቦታ ያላቸው ጥዑም የስብከት አስተምሮን ለገዳሙ ምዕመናን የሚመግቡ አዛውንት ናቸው፡፡ አባ ላዕከ ማርያም ገዳሙን ከማስተዳደር ጎን ለጎን የቅኔ መፅሃፍ መምህርም ናቸው፡፡ እድሜያቸው ገፋ ያለ ስለሆነ ምርኩዝም ያዘወትራሉ፡፡ እኚህ አበምኔት ለህይወት ቅን አመለካከት ያላቸው ፈጣሪያቸውን አብዝተው አመስጋኝ እንዲሁም ትዕዛዙን አክባሪ ናቸው፡፡ምሳሌ ለመመልከት ያህል ቀጣዩን የአባ ላዕከማርያም ንግግር መመልከት ይቻላል፡፡ "የህይወት አላማ ያለው ሰው የሚኖረው ለሙብልና ለመጠጥ ሳይሆን ለህሌናው እንዲሁም የተፈጠርንበት አላማ ለሌሎች ሰዎች ጥቅምም ነው" (ቴሎስ ገፅ 160) አባ ላዕከ ማርያም ከሃይማኖታዊ እውቀት ውጭ ፖለቲካዊ እውቀትም አለው፡፡ "ልጄ ህዝብ እንደ ህዝብነቱ ተጠያቂ አይሆንም፡፡ ለጥሩም ሆነ መጥፎ ማህበራዊ ለውጦች ተጠያቂዎቹ አስተዳዳሪዎች ናቸው፡፡ " (ቴሎስ ገፅ 132)

### 3.3.5. የአሊሰን የገፀ-ባህሪ አሳሳል በቴሎስ ረጅም ልቦለድ

አሊሰን ወጣት በሚባሉት የዕድሜ ክልል ውስጥ የምትገኝ አንድ ልጅ ያላት አሜሪካዊ ሰላይ ነች፡፡ ለሃገሯ ታማኝ እና ትጉህ ሆና ለልጇ እና ለእናቷ ያላት ቦታ ግን ከሃገሯም በላይ የሆነባት ለምትሰራቸው እያንዳንዳቸው ነገሮች ጥንቁቅና ብልህ ሴት ነች፡፡ ምሳሌ ለመመልከት ያክል “ቀላል ሴት አድርገህታል ስራዋን ካልጨረሰች በተዓምምር አትተኛም፡፡" (ቴሎስ ገፅ 115) ለጀመረችው ስራ እና አላማ እራሷን ክብሯን ሴትነቷን ጭምር ለሃገሯ አሜሪካ የቸረች ጎበዝ ሰላይ መሆኗን እንረዳለን፡፡ በሌላ በኩል ስለአሊሰን ቡቡነት ለመግለፅ ቀጣዩን ምሳሌ መመልከት ይቻላል፡፡ "አሊሰን ወደኋላ ተመልሳ ታቢልን የወሰዱበትን ቀንና ቤተሰቡ ውስጥ የነበረውን ደስታ አሰበች፡፡ በርግጥም የስራ ግዴታ ሆኖባት እንጅ በልጅ የምትጨክን አይደለችም፡፡" (ቴሎስ ገፅ 103)

### 3.3.6. የሊንዳ የገፀ ባህሪ አሳሳል በቴሎስ ረጅም ልቦለድ

ሊንዳ ከሁለት ድሃ ኢትዮጵያዊ እናትና አባቶች በአዲስ አበባ ከተማ ትምህርቷን እስካጠናቀቀችበት ጊዜ ድረስ ወጣት እና ትልቅ ተስፋ ያላት በተላይም አሜሪካ የትምህርት እድል ተሰጥቷት ስትሄድ እጅግ ደስተኛ ሴት ነበረች። ነገር ግን ለቤተሰቧ እና ለሃገሯ ልዩ ቦታ ስለነበራት የህይወት ዘመኗ ጥሩ የሚባል አልነበረም። ሊንዳ ለታቤል እናት እንድትሆን ስለታዘዘችም ሳይሆን ለልጅ ቀን እሳቤ እና ጥሩ ፍቅር ያላት በተጨማሪም ጥሩ የሳይኮሎጅ መምህርት እና በተማሪዎቿ ዘንድ ተወዳጅ ተደርጋ ተስላለች።

### 3.3.7. የታቤል የገፀ-ባህሪ አሳሳል በቴሎስ ረጅም ልቦለድ

ታቤል 33 አመት አካባቢ የሚሆነው ከአባቱ ከያሬድ እና ከናቱ ከወይዘሮ ወርቄ ተወልዶ ለቀናት ያህል በማደጎ ቤት ቀይቶ ለነመስፍን የልጅ እጦት ተብሎ ወደነመስፍን ቤት ለተወሰነ ጊዚያት እንደኖረ በአሜሪካ መንግስት ተሰርቆ አሜሪካ ወደ ሊንዳ ቤት ተቀላቀለ። ታቤል ህይወቱ ቁጥብና ከብዙ ነገሮች ተቀጥቦ ስለታሪኩ እንዳያውቅ ተኮርኩሞ አደገ። ካደገም በኋላ ባሳዳጊው ሊንዳ እንዲሁም በሚልተን እጥረት በጥሩ ሁኔታ ተምሮ እጅግ በጣም ጎበዝ የምርምር ሰውና ለሞት መድሃኒት ለመስራት መጨረሻው ደረጃላይ የደረሰ ተመራማሪ ሆኗል። ታቤል አሳዳጊውን ሊንዳን አጥብቆ የሚወድ ለናቱ ልዩ ፍቅር ያለው ወጣት ሆኖ ተስሏል።

## 3.4. ቴሎስ ረጅም ልቦለድ ከግጭት አንፃር

ሰው ከራሱ ጋር፦ ከነዚህ ግጭቶች መካከል ወርቄ በልጇ ናፍቆት ወደ ተከራይችበት ቤት ስትመለስ ሰፈር ተሰብስቦ ሲያለቅስና እልልታውን ሲያቀልጥ የሚከተለውን ምሳሌ መመልከት ይቻላል። "ቀይ ምን የሆንኩ መስሏቸው ነው እንኳን ተረፍሽ የሚሉኝ? ለምን ይሆን አንዳቸውም ስለልጃቸው ያላወሩኝ?" (ቴሎስ ገፅ 25) እያለች ከራሷ ጋር ትሟገት ነበር። የወርቄም አከራይ ወርቄ ልጇን በጠየቀች ጊዜ እንዴት ነው ለአሳዳጊ ሰጥተነዋል ብዬ የምነግራት? እያሉ ከራሷ ጋር ይሟገቱ ነበር። ወርቄ ልጇን ለማየት ወደ ማደጎ ቤት በሄደች ጊዜ ትርሲት ልጀ እያለች በምትጮህበት ጊዜ " ቀይ ምን አይነት አረመኔ ነኝ እንዴት ሰው ልጁን አጥቶ ሲሰቃይ እኔ የፈጣሪየን ስጦታ ጥዬ የምጠፋ? ምን አይነት ሰው ነኝ? " እያለች ትሟገት ነበር። (ቴሎስ ገፅ 32) በተጨማሪም በገዳሙውስጥ እራሱን ለማጥፋ ሙከራ የደረገውን ወጣት እንደምሳሌ መውሰድ ይቻላል።

ሰው ከሰው ጋር ፤ ከተፈጠሩ ግጭቶች ደግሞ ወርቄ ከማደጎ ቤት እንዲሁም ትርሲት ከማደጎቤት አስተዳዳሪዎች እና ከመስፍን ጋር የነበራት አለመግባባት በተጨማሪም አሊሰን ማንነታቸው ካልታወቁ ሰላይ አካላት ጋር የነበራት የደብዳቤ ምልልስ እንዲሁም የቃላት ምልልስ ውስጥ ጥብቅ ግጭት ነበር። አሊሰን ለመስፍን የልጁን ፎቶ ወስዳ ልጅክን እንድታገኝ እረዳሃለሁ ባለችበት ወቅት ደግሞ ከመስፍን ጋር የቀረረ ፀብ ውስጥ ነበሩ። መስፍን የልጁን ፎቶ ባሳየችው ጊዜ "ይህንን ፎት የት አገኘሽው? ልጄስ ሳሙኤል የት ነው ያለው?" ብሎ በቁጣ ሊያንቃት ተጠጋ። (ቴሎስ ገፅ 105) ሌላው ውስብስብና የከረረ ግጭት የሆነው ማንነተቸው ያልታወቁ የሽብር ቡድኖች ከነታቤል የምርምር ተቋም ላይ ያደረሱትን ጥቃት መጥቀስ ይቻላል።

ሰው ከፈጣሪው እንዲሁም ከተፈጥሮ ጋር፡- ከነዚህ ግጭቶች መካከል ስንመለከት ደግሞ በልቦለዱ ውስጥ በነታቤል የምርምር ተቋም የሞት መድሃኒት ለመስራት የሚጥሩ ተመራማሪዎች አሉ ይህንን ተግባር ሞት ተፈጥሯዊ ሁነት እንደመሆኑ ተፈጥሮን እንደመጋፋት መውሰድ ይቻላል። ታቤል ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ ታፍኖ በሚመጣበት ጊዜ ከፈጣሪው ጋር ይሟገት ነበር።

" እናቴ… እናቴ… እናቴ

እናቴ …መመኪያዬ

እናቴ …መታፈሪያዬ

የህይወት ትርጉሜ ሊንዳዬ

ምነው አንተ አምላክ

ያልጠገብኳትን እናት ነጠቅኸኝሳ?" (ቴሎስ ገፅ 12)

## 3.5. ቴሎስ ረጅም ልቦለድ ከጭብጥ አንፃር

የልቦለዱ አብይ ጭብጥ ከልቦለዱ አርዕስት ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው። " ቴሎስ ማለት የአንድ አካል አላማ ግብ እና ፍፃሜ የሚወክል ቃል ሲሆን የጥንቱ የግሪክ ፈላስፋ አርስቶትል ሙሉ ብቃትንና አንድ አካል የተፈጠረበትን አላማ ለመግለፅ ደጋግሞ የተጠቀመበት ቃል ነው። ቴሎስ የአንድ ነገር የኑረት ምክንያት ሲሆን የሰው ልጅም በስተመጨረሻ በጥረቱና ልፋቱ የሚደርስበት አላማ የግል ቴሎሱ ነው። በምድር ላይ ያሉ ድርጊቶች ሁሉ የራሳቸው ቴሎስ አላቸው። የውጊያው ግቡና አላማው ማሸነፍ ነው።" (ቴሎስ ገፅ 145) እኒህ ሀሳቦች በሊንዳ በኩል ይነሱ እንጅ ስለ አላማ በብዙ ገፀ-ባህርያት ተሰብኳል ። ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ከታች በተጠቀሰው ገፅ "የህይወት አላማውን ያገኘ ሰው ኑሮው ልክ ክሩ እንደገባለት መርፌ ሲሆን፣ክፍተትን የሚያጠብ የተለያየን የሚያገናኝ ነው። ምንም እንኳን በሀገራችን መርፌ የራሱን ቀዳዳ አይሰፋም የሚል ብሂል ቢኖርም እውነቱ ግን መርፌ የተሰራው የራሱን ቀዳዳ ሊሰፋ አለመሆኑ ነው። ደግሞም መርፌ ቅድ ባይሆን ክር ገብቶለት የሌሎችን ሽንቁር መስፋት አይችልም ነበር።" (ቴሎስ ገፅ 160) አባ ላዕከማርያም ይህንን ምክር ሲመክሩ ሁሉም ሰው የተፈጠረበት አላማ አለው ነው። ነገር ግን የልቦለዱ አብይ ጭብጥ አላማ የሚለው ሃሳብ ሳይሆን ለአላማ የሚከፈለው መስዋት ወደሚለው ሃሳብ ያጋደለ ነው። ይህን ለማለት የሚያስችለው ዋነኛ ምክንያት በልቦለዱ ውስጥ ለተፈጠሩለት አላማ ሲተጉ የሚከፍሉትን መስዋት ያስረዳል። ለምሳሌ ያሬድ የሚሎሪናን ጥቅል ትርጉም ለማግኘት 33 ዓመት ከዕድሜው ሰውቷል፣ የሚያፈቅራትን ሴት አጥቷል፣አንድ ብቸኛ ልጁን ተነጥቋል። በተመሳሳይ ሊንዳ አሜሪካ ተምራ የሳይኮሎጅ ሙህር ለመሆን ቤተሰቧን፣ሃገሯን፣ክብሯን፣ነፃነቷን እና ስሟን ለአላማዋ ከፍላለች። ስለዚህ እያንዳንዳቸውን የዋና ገፀ-ባህርያት

ምክኒያታዊነት ብንመለከት ለአላማቸው የከፈሉትን መስዋት ማገናዘብ ይቻላል። ስለሆነም የልቦለዱ አብይ ጭብጥ ለአላማ የሚከፈል መስዋዕት ነው ማለት ይቻላል።

ልቦለዱ ሌላም ንዑስ ጭብጦችን በውስጡ ይዟል ከነዚህም መካከል የፍቅርን ሀያልነት፣የልጅን ፍቅር፣የናትነትን ፍቅር፣የሃገርን ፍቅር፣የአለማዊ ኑሮን ከንቱነት፣ለሰው ክፉ ማሰብ የሚያደርሰው ተፅኖ በልቦለዱ ውስጥ እንደ ንዑስ ጭብጥ ሆነው ሰፍረዋል።

## 3.6. ቴሎስ ረጅም ልቦለድ ከመቼት አንፃር

የቴሎስ ረጅም ልቦለድ ታሪክ የተፈፀመበት አጠቃላይ ቦታ ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ለማለት አያስደፍርም። ምክንያቱም የታሪኩ ግማሽ ያህል ሁነቶች የተከወኑት አሜሪካ ኮሎራዶ ግዛት እንዲሁም ሱዳን ካርቱም ውስጥ ነው። ለዚህ ነው ብዙ ጊዜ በልቦለድ ውስጥ አጠቃላይ መቼቱን አንድ ውሱን የሆነ ሀገር ወይም ግዛት ለመጥቀስ እንከን ሊፈጥር የሚችለው። ያም ሆኖ ታሪኩ የሚጀመርበትንና የሚፈፀምበትን ቦታ መሰረት በማድረግ አጠቃላይ መቸቱን ኢትዮጵያ ነው ለማለት ይቻላል። ይህ ታሪክ የተፈፀመበተ ጊዜም እንዲሁ የ33 ዓመታትን ሁነት በልቦለዱ ውስጥ ማንፀባረቅ ችሏል። ይህም ማለት ታሪኩ የተፈፀመበት ጊዜ ከጥቅምት 1961 ዓም እስከ ጥቅምት 1994 ዓም ነው። በእነዚህም አመታት ውስጥ ብዙ ክስተቶች ተፈጥረዋል። በ 1980ዎቹ ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ግጭት በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች በየገዳማቱ ጭምር ተቀስቅሶ ነበር ። "አባ አሁን ላለው ትልቅ ግጭት ተጠያቂው ህዝቡ ወይስ አስተዳዳሪዎች? ቅድም ሰላም በጦርነት አይመጣም ሲሉ ነበር ፤ ታዲያ ጨኳኛችና ሁሉም ነገር የኔ ነው የሚሉ ሰዎች ባሉበትምድር ታግለን መብታችንን ካላገኘን ማን እንካችሁ ይለናል?" ከዚህም በላይ የሃገሪቱ ወግ ልማድ እየደበዘዘ አብሮ የመብላት ልምዱ ሁሉ መጥፋቱን መስፍን ከገዳሙ ወደ አዲስ አበባ በሄደበት ወቅት ያጋጠመው ችግር ያሳያል። "ብለው ብለው ምግብ ቤት ውስጥ ገብተው መለመን ጀመሩ? ለምን ከውጭ ሆነው አይለምኑም?" (ቴሎስ ገፅ-137) እኒህ አይነት ክስተቶች መስፍን ከገዳም ውጭ በነበረበት ወቅትም ሆነ ገዳም ከገባ በኋላ ያላያቸው ክስተቶች ናቸው።

ቴሎስ ረጅም ልቦለድ ብዙ ውስን መቼቶች አሉት ከነዚህም መካከል ወርቂና ያሬድ በፍቅር ይኖሩበት የነበረው ጎንደር ከተማ ፣ያሬድ ጥኋት ከጠፋ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ሄዳ የተከራየችበት ቤት፣ልጇን ጥላ ሄዳ ያሬድን ለመፈለግ የተጠለለችበት ገዳም፣ልጁ ከጠፋ በኋላ የሄደችበት የማደጎ ድርጅት፣አሊሰን የምትኖርበት ሃገር አሜሪካ ኮሎራዶ ግዛት፣የመስፍን እንዲሁም የትርሲት መኖርያ ቤት፣አሊሰን ለስለላ የተላከችበት ካርቱም ሆቴሉ እንዲሁም የምኝታ ክፍል፣መስፍን የመነነበት ደብረ ዳሞ ገዳም እንዲሁም የማደሪያ ጎጆ፣አሊሰን ለመስፍን የተከራየችለት ገለልተኛ ሚስጥራዊ ጎጆ መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ እያንዳንዳቸው ቦታዎች የየራሳቸው ማህበራዊ እውነታዎች አሏቸው። "መስፍን ከአድካሚ የሶስት ቀናት ጉዞ በኋላ ከልጅነቱ ጀምሮ ሊያየውና ሊጎበኘው ከሚመኘው አሁን ደግሞ ሊኖርበት ወደሚፈልገው ወደ ደብረ ዳሞ ገዳም ደረሰ። መስፍን በመነነበት ገዳም ውስጥ ብዙ መናኞችና የቅኔ ተማሪዎች ጭምር አመሻሽ ላይ የቅኔ ትምህርት በአባ ላዕከማርያም ይማራሉ። ከትምህርቱም በኋላ ለአበምኔቱ

ምስጋና ይሰጣሉ።" (ቴሎስ ገፅ-93-94) ከላይ በተጠቀሰው አንቀፅ ስለቦታውና ቦታው ስላለው ድባብ እንዲሁም ሰዎች ለቦታው ያላቸውን ክብር ስናይ ማህበራዊ እውነታዎችን መገንዘብ እንችላለን። ተጨማሪ መቸቶችን ለመግለፅ ያህል አሊሰን ሱዳን የሄደችበትን ወቅት ማንሳት ይቻላል።" ጊዜው በነዋሪዎቹ ከጥንት ጀምሮ የሚደረግ የባህል አምልኮ የሚከወንበት ወቅት ስለነበር፣ለክብረ በዓሉ መንገድ ተዘጋግቶ ስለነበር አካባቢውን ለማለፍ ብዙ ጊዜ ወሰደባቸው። በባህል ልብሳቸው ተውበው ይህን በዓል ለማክበር በካርቱም ከትመዋል።" (ቴሎስ ገፅ-68) ይህን አንቀፅ ስንመለከት ሱዳኖች አምልኮውን የሚከውኑበትን ቦታ ጊዜና አካባቢው ያለውን ድባብ ሁሉ ለመግለፅ ሞክሯል ።

በቴሎስ ልቦለድ ውስጥ ዋና ዋና ታሪኮች እንዲሁም በይዘት ሰፋ ያሉ ታሪኮች ከተፈፀሙበት መካከል ለመጥቀስ ያህል ደብረ ዳሞ ገዳም ብዙው የታሪክ ክፍል እና አንኳር ሀሳቦች በአበምኔቱ አባ ላእከማርያም እንዲሁም የመስፍን የኑሮ ውጣ ውረድ የተተረከበት በተጨማሪም የሚሎሪናን ጥቅል ክታብ ለመፍታት ኢትዮጵያዊያን ለደስታ የተሰባሰቡበት ቦታ ነው። ሌላኛው ዋና የታሪኩ አካል የሆነ ቦታ ደግሞ ኮሎራዶ ስቴት ታላቅ ጥቃት የተፈፀመበትና ብዙ ለአሊሰን ድርጊቶች ሁሉ መነሻ ቦታ ነበር። ከዛም በተጨማሪ ኮሎራዶ ዩኒቨርሲቲ የሊንዳ መግሪያ እንዲሁም በመምህርነት ያገለገለችበት ቦታ ነው። ሌላኛው የታሪኩ አካል የሆነ ቦታ የመሸሻ ቤት ሲሆን ይህ ቦታ ደግሞ ኢትዮጵያዊያን ተሰባስበው የዘመን መለወጫን የሚያከብሩበት እና ያሬድ ወርቁን ከብዙ አመታት በኋላ ያገኙበት ቦታና ስለፍቅራቸው እና ስለቆየታቸው እና ስለብሶታቸው የተጫዎቱበት የነመሸሻን ምኝታ ክፍል መጥቀስ ይቻላል።

ከላይ የተጠቀሱት በሙሉ ታሪኩ የተፈፀመባቸው ቦታዎች ሲሆኑ ድርጊቱ የተፈፀመባቸው ጊዚያት ደግሞ አሊሰን በሯ ተንኳኩቶ በበሯ ስር ደብዳቤ የሚጥሉበት ምሽቶች፣መስፍን ወደገዳም ለመሄድ በመንገድ ላይ ባለበት ወቅት ሰክሮ አሊሰን ከክንዱ መቀጣጠሪያ ያወጣችበት ምሽት፣ሱዳኖች የባህል አምልኳቸውን የሚያከብሩበት ወቅት፣ አሊሰን እንድትከታተለው ትዕዛዝ የተሰጣትን ተጠርጣሪ የቀጠረችበት ሰዓት፣መስፍን ገዳሙ ለመድረስ የፈጀበት ሶስት ቀናት፣መስፍን ከገዳሙ ወደ አዲስ አበባ አሊሰንን ለማግኘት በ1982 የሄደበት ጊዜ፣ንሃሴ1993 ሱዳን ውስጥ በተመደበው ኢትዮጵያዊ ደህንነት ስለጥቃቱ መረጃ የደረሳት ቀን፣ሰኞ ጳጉሜ 5፣1993 ዓም ያሬድና መሸሻ ለበዓልና ለሚሎሪና ፍች ቀጠሮ ዝግጅት ያደረጉበት ጊዜ፣ማክሰኞ ፣ መስከረም 1/1994 በአዲስ አመት በኮሎራዶ ግዛት መንትዮሽ ህንፃ ላይ ጥቃት የተፈፀመበት ቀን፣እሁድ፣ጥቅምት፣25/1994 ኢትዮጵያዊያን ደብረ ዳሞ ገዳም ውስጥ የተሰባሰቡበት ቀን መስፍን ልጁን የገኘበት ቀንን ጊዚያትን መጥቀስ ይቻላል። ከጊዚያትና ቦታዎች ባሻገር ዘመን ይዞ የመጣቸውን የቴክኖሎጅ እድገት ለሞት አምክንዮ እስከመፈለግ በሰርጀሪ የሰውን መልክ መቅረፅ እርስ በእርስ መተላለቅ የመሳሰሉ ክስተቶችን የመቼቱ አካል ሆነው ቀርበዋል።

## 3.7. ቴሎስ ረጅም ልቦለድ ከአንፃር አንፃር

ቴሎስ ረጅም ልቦለድ የተተረከው በሁሉን አወቅ አንፃር ሲሆን ተራኪው በሰፊ ነፃነትና የገፀ-ባህርያትን ማንነት ምኞትና ፍላጎትን አውቆ በሶስተኛ መደብ ለአንባቢ ያንፀባርቃል። ለዚህም ምሳሌ የሆኑ የአተራረክ ዘዴዎችን መቃኘት ይቻላል። ምሳሌ ስለወርቂ ምኞት ፍላጎትና ስሜት ሲገልፅ "አንጀቷን እያኘከ አላስቀምጥ ያለ የልጂ ናፍቆት ቢበረታባት እፍረቷን ትታ ወደ ሄደችበት ቤት ለመመለስ ወሰነች።" (ቴሎስ ገፅ 23) ከዚህም በተጨማሪ ወርቂ ልጇን ለማየት ወደማደጎቤት የሄደችበትን ምዕራፍ ስንቃኝ፣ "ወርቂ ከአከራይዋ ልጅ ጎን የእንግዳ ማረፊያው ጋር ተቀምጣ ፊትለፊት ባለው ወንበር ላይ የትርሲትን ለቅሶ እያየች ሆዷ ባብቷል። ከራሷ ጉዳይ ባሻገር የትርሲት ጉዳይ ያሳሰባት ይመስላል። አከራይዋ የነገሯትን ደጋግማ እያሰበች በውስጧ እንዴት አይነት ባል ቢኖራት ነው በዚህ የሃዘን ወቅት ሊያፅናናት ሊጠብቃትና ሊንከባከባት ሲገባ ሰክሮ የሚረብሻት ትላለች። መልሳ ደግሞ ለነገሩኮ ያሬድም ከዚህ አይሻልም ምንም እንኳ ባይጠጣና ባይሰክር ልጁን እንደያዝሁ አውቆ ላይመለስ ሄዷል።" (ቴሎስ፣35) በዚህ አንቀፅ ውስጥ ተራኪው የውስጧን ስሜት ምኞትና ሃሳብ ጠንቅቆ ያውቃል ለማለት ያስችላል። የተራኪውን ነፃነት የሚገልፅ ተጨማሪ ሀሳብ ለመጥቀስ ያህል " እንዴት ወላድ በአንድ ልጂ ጨክና ጥላ ትሄዳለች? ብለው የነበር ቢሆንም ቆይተው ግን የዋህነቷን እና ደግነቷን ያውቁ ስለነበር ሞታ ይሆን በማለት ጎረቤቶች ሁሉ ለሷ ተጨንቀው ነበር።" በዚህ የታሪክ ሃሳብ ውስጥ ተራኪው በአባሪ ገፀ ባህርያት የወርቂን ውስጣዊ ማንነት ለአንባቢያን አቅርቧል።

የአተራረክ ዘዴውን እውን ከሚገልፁ ሃሳቦች መካከል ተራኪው የራሱን ሃሳብ የሚያንፀባርቅበትን መንገድም ለመመልከት ያህል ቀጣይ ሀሳቦችን መዳሰስ ይቻላል። ለምሳሌ ያህል ከታች በተገለፀው ገፅ "መስፍን በቤተክርስቲያኑ ቅጥር ውጭ ቆሞ ሲሰብክ ወቅቱ በሃገሪቱ ክፍሎች የከፋ ጦርነት በመሆኑ ሰላም የሚለው ቃል የሰውን ጆሮ እየጠለፈ ወደሱ ያከማቻቸው ነበር።" (ቴሎስ ገፅ 138 ) "አሊሰን ትንሽ ፍርሃትና ግራ ቢገባትም መስፍንን አውርታ ለራሷ መጠቀሚያ ለማድረግ አሰበች። እንዴት እንደምታወራው ግራ ቢገባትም ስለምትለው ነገር ሁሉ መዘጋጀት ጀመረች። " (ቴሎስ፣104) በነዚህ መሰል የተራኪው ነፃነቶች ሁሉ ታሪኩ የሁሉን አወቅ አንፃር ባህሪያት እንዳሉት ማወቅ ይቻላል።

## 3.8. የቴሎስ ረጅም ልቦለድ ጠንካራ ጎን

ብዙ ደራሲዎች ከሚፅፉት ማነኛውም የስነ ፅሁፍ ዘርፍ ትልቅ ችግር የሴራ ማነስ ነው ማለት ይቻላል ።ይህ ልቦለድ ግን ከብዙ ልቦለዶች በተለየ በርከት ያሉ ትልሞች አሉት ። ከነዚህም መካከል የወርቂና የያሬድ ፍቅር፣ የሚሎሪና ፍች ፣የታቤል መሰረቅ፣ የመስፍን የገዳም ህይወት፣የአሊሰን ሚስጥርና የስለላ ሁኔታ፣ የአሽባሪዎች ተግባራትና ሌሎችም ትልሞችን አጣምሮ ይዟል። የዚህ ልቦለድ ሌላኛው ጠንካራ ጎን ደግሞ ሰፋ ያሉ ሃገራዊ ጭብጦችን አዳዲስ ሀሳቦችን ለምሳሌ ስለ ባህል መድሃኒት እንዲሁም እፀ መሰዎር የአንባቢን ቀልብ የሚስቡ ሃሳቦችን ለአንባቢ አንፀባርቋል።

## 3.9. የቴሎስ ረጅም ልቦለድ ደካማ ጎኖች

ልቦለዱ ከአላባዊያን አንፃር ሲታይ ደካማ ጎኑ ከእያንዳንዱ አላባዊያን ህፀፅ ይታይበታል። ከነዚህ ህፀፆች መካከል ምሳሌ ለማንሳት ያህል ገፀ-ባህሪያት የቀረቡበት መንገድ ቀለል ብለው ትኩረት በማይሰብ መንገድ ነው። ይህም ማለት

አንባቢው ገፀ-ባህሪውን ለመውደድም ለመጥላትም በቂ አቀራረብ እና ምክኒያታዊነት ይጎላቸዋል። የበለጠ ግልፅ ለማድረግ ያክል አቀንቃኝ እና ፀረ-አቀንቃኝ ገፀ-ባህርያት ገፀ-ባህሪው በሚፈልገው መጠን አልተቀረፁም። ምሳሌ ለማንሳት ያክል የወረቁ ገፀ-ባህሪ አቀራረብ የምታደርጋቸው ድርጊቶች እና ምላሻቸው ድባብ ከባድ ሀዘን ቢሆንም አንባቢን የማሳዘን አቅም የላቸውም። ይህ ደግሞ የገፀ-ባህሪ አቀራረብ ችግር ነው። ሌላኛው ጉድለት ደግሞ የታሪኩ ባለቤት ማነው ለሚሰኝ ጥያቄ ልቦለዱ ላይ ግድፈት ይታይበታል። ይህም ማለት ሁሉንም ገፀ-ባህርያት ታሪኩን ከፋፍሎ እኩል በሚባል መጠን ስለሰጣቸው ለታሪኩ ባለቤትነት የተመረጡ ገፀ-ባህርያት መብዛታቸው የታሪኩን ጉዘት በትነውታል። የገፀ-ባህሪያት መብዛት ደግሞ በልቦለድም ሆነ በሌላ የስነፅሁፍ ዘርፍ እንደ ደካማ ጎን መውሰድ ይቻላል። በተላይ በተላይ ደግሞ የልቦለዱ አንኳር ችግር የሆነው የፀረ አቀንቃኝ ገፀ-ባህርያት ማነስ ነው።

ሌላኛው ደካማ ጎን ትልሙ መብዛቱ ብቻ ጠንካራ ጎን ሊሆን አይችልም ታሪክ ግጭት ከሌለው ብቁ ትልም ሊሆን አይችልም። ይህ ደግሞ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የፀረ-አቀንቃኝ ገፀ-ባህርያት ማነስ ነው። ምሳሌ ለማንሳት ያክል ልቦለዱን ስንዳስሰው ብዙ ገፀ ባህሪያት አቀንቃኝ እና ዋና ገፀ-ባህርያት ሆነው ሌላ አቻ ተፃራሪ ሀይላት ከሌላቸው ግጭቱ ልል ሆኖ ለአንባቢ ልብ የሚሰቅል ታሪክ ማድረግ አይቻልም። ይህም ማለት ወና ገፀባህርያትን እነ መስፍንን፣ወርቄን፣አባ ላእከማርያምን፣ሊንዳን ፣ታቤልን ብንወስድና ለነሱ አቻ የሚሆን አሳማኝ ተፃራሪ ሃይል የላቸውም።

ሌላኛው የልቦለድ አላባዊያን ደግሞ አንፃር ነው። የዚህ ታሪክ አንፃር ታሪኩ የተተረከበት መንገድ በሁሉን አወቅ አንፃር እንደመሆኑ አንባቢው በትረካው ወቅት ከገፀ-ባህርያት ጋር አሊያም ቀድሞ ታሪኩን ማወቁ ልቡ የሚጭረውን የጉጉት ስሜት ይቀንሰዋል ። ምሳሌ ለመውሰድ ያክል ከታች በተገለፀው ገፅ ውስጥ ስንመለከት " ታቤል አድጓል፣ሊንዳም የዶክትሬት ትምህርቷን አጠናቃ በዩንቨርስቲው ማስተማር ጀምራለች። ዛሬደግሞ ከወትሮው ማለዳ ተነስታ ወደ ዩንቨርስቲ ለመሄድ እየተሰናዳች ነው።" ሁነቶችን ቀድሞ ከማሳዎቅ ይልቅ ታሪኩ መከሰት ባለበት እድሜ ቢታወቅ ለአንባቢ ስሜት ሰጭ ይሆን ነበር። ተጨማሪ የልቦለዱ ደካማ ጎን ደግሞ የትረካው አሊያም የታሪኩ ጉዘት እንዳለ ሆኖ ፁሁፋ ኪነታዊ ለዛ ይጎለዋል። ይህም ማለት ድርሰቱ የቀረበበት መንገድ እንዲሁ የሰው ልጅ በለት ከእለት ኑሮው በዘፈቀደ የሚጠቀመውን የቋንቋ ስርአት ተጠቅሟል። ይህ ደግሞ አንባቢው በታሪኩ ውስጥ የሚፈልገውን የተለየ ነገር የማግኘት እድሉን ያሳጣዋል ማለት ነው። ምሳሌ ብንወስድ የልቦለዱ ታላቅ ፍልስፍና ተብለው የተወሰዱት" በህይወቴ የሚያስደስተኝና የሚቀለኝ ስራ ምንድን ነው? ፣ እኔ ምን አይነት ችሎታ አለኝ? ፣ ወደፊት በህይወቴ ምን አይነት ነገሮችን መስራት እፈልጋለሁ?" (ቴሎስ ገፅ 149-151) እነዚህ ጥያቄዎች በየሳይኮሎጅው መፅሃፍ እንዲሁም በየቤቱ ሰው እራሱን እየጠየቀ ለዘመናት ሲመልሳቸው የኖሩ ሃሳቦች ናቸው። ነገር ግን በልቦለዱ ውስጥ እንደ ትልቅ ጥያቄ ተደርገው ከፍተኛ የሆነ ተለምዷዊ ማብራሪያ ሰፍሮላቸዋል። እነዚህ የተለመዱናየተሰለቸ ሃሳብም ሆነ የቋንቋ አጠቃቀም የሰውን አዕምሮ የማሰልቸትና የማቻክ ሃይል አላቸው ።

## ምዕራፍ አራት

## 4.ማጠቃለያ

*ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በቴሎስ ረጅም ልቦለድ ውስጥ የልቦለድ አላባዊያንን በመተንተን ለእያንዳንዱ አላባዊያን ገለፃና ትንታኔ ለመስጠት ሞክሯል። በተጨማሪም ጥናቱ የልቦለዱን አላባዊያን ደካማና ጠንካራ ጎን ምክኒያታዊ በሆነ*

መንገድ ሂስ ለማድረግ ሞክሯል። ጥናቱ  የዳሰሳቸው እያንዳንዳቸው ሃሳቦች ለደራሲው ደርሰው ለውጥ መፍጠር ባይችሉም ስለ ልቦለድ አላበዊያን በቂ ትንታኔን በመስጠት እረገድ ጥናቱን ለሚመለከቱ ሁሉ ጥሩ ግንዛቤ መሆን ይችላል።

ብሎም መፅሃፉ ያነሳው ሃሳብ አንድ ሰው ለአላማው መክፈል ያለበትን መስዋት በረከት ባሉ አቀንቃኝ ገፀባህርያት በኩል ጠቁሟል። ቴሎስ ረጅም ልቦለድ ሙሉ አላባዊንን ስንዳስስ በገፀባህሪያት በኩል አቀራረፃቸውም ሆነ አቀራረባቸው ዝቅ ያለ፣ በርከት ያሉ  ትልሞችና ልል ግጭቶች ያሉት፣ጠንከር ያለጭብጥ ያለው፣ በጣም በብዙ መቼቶች የተከወነ ፣ ትኩረት የሚስብ ታሪክ ኖሮት ግን አተራረኩ ግልፅ ሆኖ ለአንባቢ ምርምር የማይሆን አንፃር ተጠቅሟል።

ቴሎስ ረጅም ልቦለድ በዚህ መልክ ተደርሶ ለአንባቢ መድረሱ  ደራሲያንም ሆነ አንባቢያን በድክመቱም ሆነ በጠንካራ ጎኑ ጥሩ እውቀት የሚሸምቱበት ልቦለድ ሆኖ ቀርቧል ። ጥናቱም እንደ አንድ የመፅሃፉ አካል በመሆን የድርሰቱን አላባዊያን ፣ጠንካራና ደካማጎን  ለመቃኘት ሞክሯል።

## 4.1. የመፍትሄ ሀሳቦች

አጥኝው ቴሎስ ረጅም ልቦለድን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ልክ መረጃዎችን በማጣቀስ ከአላባዊያን አንፃር ተንትኗል። ሆኖም አጥኝው በልቦለዱ ውስጥ ቢስተካከሉ ሚላቸው አንኳር ሃሳቦችን ከዚህ በታች አስፍሯል።

ቴሎስ ረጅም ልቦለድ እንደ እረጅም ልቦለድነቱ አላባዊያንን ያዋቀረ ቢሆንም እያንዳንዱን አላባዊያን ነጣጥለን ለማየት ስንሞክር ግን ክፍተቶች ይታዩበታል። ታሪኩ የአንባቢን ቀልብ ከጅማሬው እስከፍፃሜው በጉጉት መያዝ እንዲችል አላባዊያንን ከዚህ በላይ ቢጠነክር፤ ፀረ-አቀንቃኝ ገፀባሕርያትን በአቀንቃኝ ገፀባሕርያት ልክ ቢቀርፃቸው አቻ የሆነ ጠንካራ ግጭት ኖሮት ልቦለዱ ከዚህ ይበልጥ ትኩረት ሳቢ ይሆን ነበር። በተጨማሪም ገፀባህርያትን መጥኖ የቋንቋ አጠቃቀሙን ረቀቅ ያለ ኪነታዊ ለዛ የተጎናፀፈ ቢያደርገው ያነሳውን ታሪክ በሚገባው ልክና እንደ ሃሳቡ ክብደት አፅኖት ተሰጥቶት መቃኘት ይችል ነበር።

# ዋቢ-መፅሃፍት


መላኩ ተሰፋ። "ግራጫ ቃጭሎች ረጅም ልቦለድ ከገፀባህርያት አሳሳል አንፃር"። ጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ 2012 ዓ.ም።

ሰብለወርቅ አጉማሴ። "ተልሚድ ረጅም ልቦለድ ከልቦለድ አላባዊያን አንፃር"። ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ፣2013 ዓ.ም ።

ሳሙኤል ተሰፋዬ ። "የትወና ጥበብ።" አዲስ አበባ፣ሄራቴጅ ማተሚያ ቤት፣2010 ዓ.ም።

ብርሃኑ ገብረ-ፃዲቅ። "አጠቃላይ የአማረኛ ቋንቋ።" በረከት ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማ፣ 2008 ዓ.ም።

ያለው እንዳወቀ ሙሉ ። "የምርምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር።" ሊትማን መፅሃፍት፣2009 ዓ.ም።

አለም እሸቱ። "መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ ዘዴ።" አዲስ አበባ፣ብ/ሰ/ማ/ቤት፣2001 ዓ.ም።

ወንድወሰን ሙሉጌታ። "የዋና ገፀባህርይ አሳሳል በአውሎንፋስ ዳንኪረኞች ረጅም ልቦለድ ውስጥ።'' አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ፣2001 ዓ.ም።

ናሁሰናይ ፀዳሉ። ''ቴሎስ ረጅም ልቦለድ።'' አዲስ አበባ። ሮኖቦት አታሚዎች፣2014 ዓ.ም።

ዘሪሁን አስፋው። ''የስነ-ፅሁፍ መሰረታዊያን።'' አዲስ አበባ፣አርቲስት ማተሚያ ቤት፣ 2005 ዓ.ም።